# በደጋ ዳሞት ወረዳ የእረኞች ግጥም ይዘት ትንተና

በ

ሙሉቀን ጌትነት

ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍል  ለአርትስ ባችለር ዲግሪ
ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ

አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ
ሰኔ 2001 ዓ.ም

# በደጋ ዳሞት ወረዳ የእረኞች ግጥም ይዘት ትንተና

በ

በሙሉቀን ጌትነት

አማካሪ፡- አየለ ፍቅሬ

ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ
ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ

አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ
ሰኔ 2001 ዓ.ም

# ምስጋና

ብዙ መከራና ችግሮችን አሳልፎ ለዚህ ያበቃኝ ጌታ ኢየሱስን አመሰግናለሁ፡፡ እንዲሁም ካላቸው የተጨናነቀ ጊዜ ውስጥ ሳይሰለቹ ለእኔ ጊዜ በመስጠት ስራየን ላረሙልኝ አማካሪዬ ለአቶ አየለ ፍቅሬ ምስጋናዬ ከፍ ያለነው፡፡ እንዲሁም ሳይሰለቹ ዛሬም ድረስ እርዳታቸው ላልተለየኝ ቤተሰቦቼ በሙሉ እና በሀሳብም ሆነ በምክራቸው ከጐኔ ላልተለዩኝ ጓደኞቼ ለMARS ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

ይህን የጥናት ወረቀት በተጣበበ ጊዜ በፍጥነት ለተየበችልኝ ወ/ሪት ራሔል ላቀው ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

# ማውጫ

**አርዕስት** **ገጽ**

*ማውጫ* ……………………………………………………………………………………… *ሀ*
*ምስጋና* ………………………………………………………………………………………… *ለ*
ምዕራፍ አንድ ........................................................................................1
1. የጥናቱ መቅድሞች ..................................................................................5
1.1. የጥናቱ ዳራ ...........................................................................................5
1.2. የጥናቱ አላማ.........................................................................................7
1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት ...............................................................................7
1.4. የጥናቱ ዘዴ ...........................................................................................7
1.5. የጥናቱ ወሰን .........................................................................................8
1.6. የጥናቱ አደረጃጀት ..................................................................................8
1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና ለችግሮቹ የተሰጡ መፍትሄዎች .....................8
1.8. ለችግሮቹ የተሰጡ መፍትሄዎች ................................................................9
ምዕራፍ ሁለት ........................................................................................10
2. ክለሳ ድርሳናት.......................................................................................10
2.1.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት .........................................................................10
ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ........................................................................................13
2.2. የቃል ግጥም ምንነት ..............................................................................13
2.3. የቃል ግጥም አከዋወን.............................................................................14
ምዕራፍ ሦስት..............................................................................................16
3. የእረኛ ግጥም ይዘት ትንተና........................................................................16
3.1. የእረኞች ምንነት.....................................................................................16
3.2. የጅራፍ ግጥሞች ...................................................................................17
3.3. የስድብ ግጥሞች......................................................................................19
3.3.1. የአህያ መጣች ግጥሞች ..........................................................................19
3.3.2. የእንካ ስላንትያ ግጥሞች .........................................................................21
3.3.3. ልዩ ልዩ የስድብ ግጥሞች.........................................................................24
3.4. የወዘበሪታ/የቀልድ/ ግጥሞች.......................................................................26
3.5. ብሶትን የሚገልፁ ግጥሞች .......................................................................30
ማጠቃለያ....................................................................................................33
ሙዳየ ቃላት ................................................................................................34
ዋቢ መፃሕፍት ...............................................................................................35
**አባሪዎች**
አባሪ አንድ
አባሪ ሁለት

# ምዕራፍ አንድ

# 1. የጥናቱ መቅድሞች

## የጥናቱ ዳራ

ደጋዳሞት በምዕራብ ጐጃም ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች አንዱ ነው፡፡ ወረዳው ከአዲስ አበባ 391 ኪ.ሜ በምዕራብ፣ ከባህር ዳር ደግሞ 266 ኪ.ሜ በምስራቅ በኩል ይገኛል፡፡ ወረዳው በስተሰሜን ከቢቡኝ ወረዳ፣ በስተደቡብ የጃቢጠህናንና የደምበጫ ወረዳዎች፣ በምስራቅ የደምበጫ ወረዳ፣ በምዕራብ የቋሪትና የቢቡኝ ወረዳ ያዋስነዋል፡፡

ከወረዳው ማስታወቂያ ጽ/ቤት ያገኘሁት መረጃ እንደሚያመለክተው በወረዳው ውስጥ የሰፈረው ህዝብ ቁጥር 197,007 ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በወረዳው ውስጥ ያለው የነዋሪ ቁጥር እየጨመረ መሄዱን ያገኘሁት መረጃ ያሳያል፡፡ በወረዳው ውስጥ 32 ቀበሌዎች አሉ፡፡ ከእነዚህም 32 ቀበሌዎች መካከል አንድ የከተማ ቀበሌ አለ፡፡ በዚህ የከተማ ቀበሌ ውስጥ የሚኖረው የህዝብ ቁጥር 3,474 የሚሆንነው፡፡ በወረዳው ውስጥ ያሉ 31 የገጠር ቀበሌዎች የህዝብ ቁጥር ብዛት ደግሞ 193,533 የሚሆን ህዝብ እንዳለ ከወረዳው ማስታወቂያ ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

ደጋዳሞት ደጋ ነው፡፡ ደጋዳሞት የሚለውን ስያሜ ያገኘውም ደጋ ከመሆኑ የተነሳ ነው፡፡ ወረዳው በአንዳንድ ወቅት ከተለመደው በላይ ቅዝቃዜ ይታይበታል፡፡ በህዳር እና በታህሳስ ያለው ቅዝቃቄ ከሌላው ጊዜ የተለየ ነው፡፡ በእነዚህ ወቅቶች የአካባቢው መሬት በሙሉ በውርጭ ይሸፈናል፡፡ የአካባቢው ነዋሪ ቅዝቃዜውን የለመደው ቢሆንም እንዳንድ ጊዜ ከበረታ ሙቀትያላቸውን ልብሶች ይለብሳል፡፡ ከየልብሱ ቁርጥራጭ በሚያያዝና በመስፋት ድሪቶ፣ ካፖርት፣ጎጃምአዘነ ወዘተ ይለብሳሉ፡፡

በወረዳው የተለመደው የቤት አሰራር ቆርቆሮ ቤት እና ጎጆ ቤት ነው፡፡ ጎጆቤት ግድግዳው ከእንጨትና ከጭቃ ጣሪው ከገብስ ብርዕ የሚሰራ ሲሆን ቆርቆሮ ቤት ግድግዳው ከእንጨትና ከጭቃ፣ ጣሪያው ላይ ቆርቆሮ በመምታት ይሰራል፡፡ ቆርቆሮ ቤት ሲያረጅ እንዳይወድቅ በማሰብ በግርግዳው ዙሪያ ድንጋይ ይከቡበታል፡፡ ቆርቆሮቤት በአካባቢው ዋና መኖሪያ አድርገው ይጠቀሙታል፡፡ ቆርቆሮ ቤት ያለው ሰው ሁሉ ጎጆቤት አለው፡፡ ጎጆ ቤት በአሁኑ ጊዜ እንደ ማብሰያ ቤት የሚጠቀሙት ቢኖሩም ዋና መኖሪያ ቤት ያደረጉት ብዙዎች አሉ፡፡

እነዚህ ቤቶች በውስጣቸው የተለያዩ ክፍሎችን የያዙናቸው። የከብቶች ማደሪያ፣ የመኝታ ክፍል፣ የመገልገያ ዕቃዎች ማስቀመጫና ሌሎችንም የያዙ ናቸው።

በወረዳው የሚኖረው ህዝብ በብዛት በግብርና ስራ የሚተዳደር ነው። በወረዳው ገብስ፣ ድንች፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ባቄላ፣ አተርና በቆሎ ይመረታል። ከነዚህ በተጨማሪ ሌሎች የቅባት እህሎች፤ ተልባ፣ ኑግ፣ ጕመንዘር የመሳሰሉት ይመረታሉ። የአካባቢው ነዋሪ በአመት ሁለት ጊዜ ያመርታል። ከዚህ የተነሳ ኑሮውን በማብቃቃት ይገፋል። ስለዚህ የእርሻ ወቅት ካለፈ በኋላ ገበሬው ተጨማሪ ስራ ለመስራት ይገደዳል። በዚህም ምክንያት ወደተለያዩ አካባቢዎች በመሄድ ጫካ መንጥሮ ያርሳል። ወይም እንደ አናጢነት፣ ግንበኝነት፣ የመሳሰሉ የእጅ ስራዎችን ተቀጥሮ ይሰራል።

በደጋ ዳሞት ውስጥ የጋማ ከብቶች፣ የቀንድ ከብቶች፣ በግና ፍየል እንዲሁም ሌሎች የቤት እንስሳት አሉ። ወረዳው ደጋ ከመሆኑ የተነሳ በግና ፈረስ ለማርባት አመች በመሆኑ ከሌላው አካባቢ በተሻለ ሁኔታ በወረዳው በብዛት ይገኛሉ። የአካባቢው ነዋሪ አምርቶ ከሚያገኘው ገቢ በተጨማሪ ከብቶችን፣ በጎችን፣ ፈረሦችንና ፍየሎችን በማርባት ተጨማሪ ገቢ ያገኛል።

ከላይ እንደተጠቀሰው የጋማ ከብቶች፣ የቀንድ ከብቶች ፍየልና በጎችን የሚያግዱ እረኞች አሉ። እረኞች ከብቶችን ግጦሽ ወዳለበት ቦታ ያሰማራሉ። በዚህ ጊዜ ከተለያዩ ቦታዎች የሚሰበሰቡ እረኞች በጋራ ይጫወታሉ፣ ይዘፍናሉ፣ ሀዘናቸውን ደስታቸውን በስነቃል ሲገልፁ ይሰማሉ።

ስነቃል የአንድ ማህበረሰብ ባህል፣ ታሪክ፣ የህይወት መልክ የሚያስተላልፍ በመሆኑ በወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ እረኞች የዕለት ተዕለት ህይወት ለማሳየት ጥናቱ በስነቃል ላይ ሊመሰረት ችሏል። ከዚህ በተጨማሪ ወረዳው ለዚህ ጥናት የተመረጠበት ምክንያት ለአካባቢው ቅርበት ስላለኝ መረጃ የት አካባቢ ማግኘት እንዳለብኝ ስለማውቅ ነው።

ይህን ጥናት እንዳጠና አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች አሉ። ደጋ ዳሞት ወረዳ ከሚገኙ ቀበሌዎች ውስጥ በአንዱ አንድ አባል ሆኘ አድጌአለሁ። ስለዚህ የዚህ አካባቢ እረኞች በህብረተሰቡ ዘንድ ያላቸውን ቦታ፣ ህብረተሰቡ ለእነሱ ያለውን አመለካከት የነበርኩበት አካባቢ በመሆኑ አውቀዋለሁ። ይህም በእረኛ ግጥም ውስጥ ሊዳሰስ የሚችል ማህበራዊ ጉዳይ አለ ብዬ ስላሰብኩ በዚህ ርዕስ ላይ ጥናቴን እንድሰራ አነሳሽ ምክንያት ሆኖኛል።

## 1.2. የጥናቱ አላማ

በወረዳው ውስጥ ያሉ እረኞች በግጥማቸው በሚያነሷቸው ጉዳዮች መሰረት በይዘት ከፋፍሎ በመተንተን የሚያስተላልፉትን መልዕክት ለሌሎች ማሳየት፣ በዚህ ወረዳ የእረኛ ግጥሞች ላይ የተደረገ ጥናት ባለመኖሩ ግጥሞቹን ስብስቦ ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለትምህርት የኢትዮጵያን ባህል እንደመዳሰሱ መጠን ይህም ጥናት ለዚህ ክፍለ ትምህርት ከስነቃል አንፃር የዚያን አካባቢ ህዝብ ባህልና ወግ፣ እንዲሁም እረኞች የሚያስተላልፋትን የቃል ግጥም ሰብስቦ በማስቀመጥ ወይም ቀርሶ ማስቀመጡ አስተዋፅኦ ያደርጋል ብዩ በማሰብ ነው፡፡ በመሆኑም ስለደጋ ዳሞት እረኞች ማንነት፣ ፍላጐትና ማህበራዊኑሮ የሚው ነገር ስላለ፣ እንዲሁም ወደፊት ለሌሎች አጥኝዎች በወረዳው ላይ በመመስረት የእረኛ ግጥሞች ላይ ጥናት ለማድረግ ቢነሱ ይህ ጥናት እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ዘዴ

ይህን ጥናታዊ ጽሑፍ ለማቅረብ የተጠቀምኩበት የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ በሁለት መልኩ ነው፡፡ አንደኛው እረኞች ከሚገኙበት ቦታ በመሄድ በመቅረፅ ድምፅ አማካይነት የመስክ ጥናት ተደርጓል፡፡ ሁለኛው ደግሞ ከእረኞች ያገኘኋቸውን ግጥሞች ቃል በቃል በመፃፍ መረጃ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ በወረዳው ውስጥ ካሉ 32 ቀበሌዎች በ11 ላይ መረጃ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ መረጃው የተሰበሰበባቸው ቀበሌዎች አረፋ ደብተራ፣ አበግራ፣ ሽምብርማ፣ ሻንጊ ደረቄ፣ ፈረስ ቤት ሚካኤል፣ ዝቋላ፣ ቋቁቻ፣ ወገም፣ ድኩልካና፣ ጠሊምና ፍላጢት፣ ናቸው፡፡ እነዚህ ቀበሌዎች ሊመረጡ የቻሉት ተወልጄ ካደኩበት ቀበሌ ጋር ቅርበት ያላቸው መሆኑ እና ካለኝ ጊዜ አኳያ ሌሎች ራቅ ያሉ ቦታዎች መሄድ ስላልተቻለነው፡፡

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ገላጭ በሆነ መንገድ የሚያቀርብ ነው፡፡ ገላጭ በሆነ መንገድ የቀረበው የእረኛ ግጥም የሚያስተላልፈውን መልዕክት ለማሳየት ትንተና ያደርጋል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በምዕራብ ጐጃም ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች አንዱ በሆነው በደጋዳሞት ወረዳ ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወረዳው ውስጥ የሚገኙ የእረኛ ግጥሞችን በመተንተን ላይ የተወሰነ ነው፡፡

## 1.6. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት ለሦስት ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ በመጀመያ ምዕራፍ የጥናቱ መግቢያ ቀርቧል፡፡ ይህም የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች(ዳራ)፣ ዓላማ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ ወሰን፣ አደረጃጀትና በመስክ ሥራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችንና ለችግሮቹ የተሰጡ መፍትሄዎችን አካትቷል፡፡

በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ስራዎች ቅኝትና ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ይዟል፡፡ በተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ትስስር ያላቸውና በተለያዩ ደረጃዎች የተሰሩ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች ተዳስሰዋል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች ጥናታዊ ስራዎች ተቃኝተውበታል፡፡ በንድፈ ሀሳባዊ ዳራው ደግሞ ለዚህ የምርምር ሥራ ደገፉ የሆኑ የምሁራን አስተሳሰቦች ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ ሦስት የጥናቱዋነኛ አካል ሲሆኑ በመስክ ስራ ላይ በምልከታና በቃለ መጠይቅ የተገኙ ልዩ ልዩ መረጃናዎች ከጥናቱ ንድፈሀሳብ አኳያ ሰፋ ያለ ገለፃና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በትንተናው ላይ የተነሱ አንኳር ነጥቦችን ተመርኩዞ በጥናቱ መጨረሻ ማጠቃለያ ተሰጥቷል፡፡

## 1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና ለችግሮቹ የተሰጡ መፍትሄዎች

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በተሰበሰቡበት ወቅት ብዙ ችግሮች ነበሩ፡፡ ከእነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

1. ለመጀመሪያ ጊዜ እረኞች ባሉበት ቦታ በመገኘት እንዲነግሩኝ ስጠይቅ አናውቅም የካሴትዘፈን ብቻ ነው የምናውቀው ማለት፣
2. እረኞች መቅረፀ ድምፅ ላይ ለመናገር መፍራት፣ መቅረፀ ድምፁ ወደ እነርሱ ሲቀርብ የሚናገሩት ሀሳብ መጥፋት፣

3. አንዳንድ በዕድሜ ትልቅ የሆኑትና ሌሎችም ግጥሞቹን ሰብስብሽ ልትሸጪ፣ ልትዘፍኝ ነው በማለት ግጥሞችን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸው በጥናቱ ወቀት ካጋጠሙ ችግሮች የተወሰኑት ናቸው፡፡

## 1.8. ለችግሮቹ የተሰጡ መፍትሔዎች

1. እረኞች የሚችሉትን ከካሴት ዘፈን ውጭ የሆነ ዘፈን እንዲነግሩኝ ማድረግ፣
2. ድምፃቸውን በምቀርፅበት ጊዜ መቅረፀ ድምፁን ሳይመለከቱ እንዲዘፍኑ ማድረግ፣
3. ግጥሞቹን ለዘፈን ሳይሆን ለትምህርት ቤት እንደፈለኳቸው በማስረዳት ያጋጠሙኝን ችግሮች ተቋቁሜ ግጥሞቹን ልሰበስብ ችያለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# 2. ክለሳ ድርሳናት

## 2.1.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

እስካሁን ባየኋቸው ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለድግሪ ማሟያ ከቀረቡት ጥናቶች መካከል ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚገናኙት ሁለት ጥናቶች ናቸው፡፡ ሌሎች በተዘዋዋሪ ከዚህ ስራ ጋር የሚዛመዱ ሦስት ስራዎች አሉ፡፡ እነዚህ ሦስቱ ጥናቶች በስራ ግጥም ላይ የተሰሩ ናቸው፡፡

"የጊምባ እረኞች የሚያሰሟቸው ግጥሞች"(1982) በሚል ርዕስ በሺር ፈለቀ ጥናታዊ ጽሑፉን አቅርቧል፡፡ በሺር በወሎ ክፍለሀገር በወር ሂመኖ አውራጃ በለጋሞቦ ወረዳ የሚገኙ "የጊምባ" የአማርኛ ተናጋሪ እረኞች የሚያሰሟቸውን የጅራፍ ግሪፊያ፣ የእንካ ስላንትያና የአህያ መጣች ግጥሞችን በመሰብሰብ ይዘትና ቅርፃቸውን ተመልክቷል፡፡ በስራው ትኩረት ያደረገው ግጥሞችን በመሰብሰብ ይዘትና ቅርፃቸውን ተመልክቷል፡፡ በስራው ትኩረት ያደረገው ግጥሞቹ የሚገጠሙበትን ዳራና ይዘታዊፋይዳ በማብራራት ሲሆን ቅርፃቸውን በተመለከተ አሰነኛኘትና ግጥሞቹ የሚያሳዩትን ድግግሞሽ ባጭር ባጭሩ ይጠቅሳል፡፡

በአጠቃላይ በሺር ከካላይ የተጠቀሱት ሦስት ግጥሞች ብቻ የጊሞባን ህብረተሰብ ህይወት የሚዳስሱ አይደሉም በማለት ይገልፃል፡፡ እረኞቹ በጨዋታ መልክ የሚያነሷቸው ግጥሞች ሁሉንም ነገር አጠቃላሎ ይይዛል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ስለዚህ የጊምባን ማህበረሰብ ስነቃል አስባስቦ ለቅርስነት ለማብቃት ጥረት የሚያደርጉ ወገኖች ይህን ዝግጅት ለመንደርደሪያነት ይሆናል በማለት ጥናቱን አጠቃልሏል፡፡

የበሺር ጥናታዊ ጽሑፍ አላማ በጊምባ የእረኛ ዘፈን ግጥሞች የሚያስተላልፋትን መልዕክት ማሳየትና የእረኛ ግጥሞችን ሰብስቦ ለተተኪው ትውልድ ለማስተለለፍ ሲሆን እነዚህን ነገሮች ማድረጉ ጥናቱን በተወሰነ መልኩ ግብ መች እንደሆን አድርጐታል፡፡

"የአክሱምና አካባቢዋ እረኞች የሚያሰሟቸው የዘፈን ግጥሞች"(1990) በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሑÕን ያቀርበ ተኸላይ ትዕዛዙ ነው፡፡ ተኸላይ በትግራይ ክልል ሰሜናዊ ምዕራብ አቅጣጫ በምትገኘው አክሱም ላይ የሚገኙ እረኞች የሚያሰሟቸውን የአውዳመት ግጥሞች፣ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ የሚገጥሟቸውን ግጥሞች በመሰብሰብ ከይዘትና ከቅርፅ አንፃር ተመልክቷል፡፡ በስራውም ትኩረት ያደረገው የግጥሞቹን ይዘት

መተንተን ላይ ሲሆን ግጥሞቹ ከቅርፃቸው አንፃር አሰነኛኘት፣ የሐረግ ምጣኔ፣ ቤትአመታትና የዘይቤ አጠቃቅምን አሳይቷል።

ተኸላይ በአጠቃላይ በአክሱም አካባቢ ያለውን ማህበረሰብ አመለካከት፣ እምነት፣ ፍላጐት፣ ባህል ያሳያል። በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ ስነ ምግባሮች፣ ሐቀኝነትን፣ ውሸትን፣ እንዲሁም ህብረተሰቡ ስለወሲብ ያለውን አመለካከት፣ ህብረተሰቡ በእረኞች ላይ ያለውን አመለካከት፣ በጥናቱ ውስጥ ጠቅሷል።

ከዚህ በተጨማሪ ስለ ዜማ አጠቃቀማቸው "የ"ን በግጥም ወይም በሀረጐችና በስንኞች መጨረሻ ላይ መጠቀም ዜማን እንዲያገኙ ያደርጋል በማለት ያነሳቸው ሀሳቦች በጥናቱ የሚታዩ ጠንካራ ጐኖች ናቸው።

በዚህ ጥናት ውስጥ የሚታየው ድክመት ጥናቱ የሚያተኩረው ቃል ግጥም ላይ እንደመሆኑ ስለቃል ግጥም ምንነት የሚገልፁት ነገር አለመኖሩ ነው።

ተኸላይ የጥናቱ አላማ ግጥሞቹ ስለ አክሱም ህብረተሰብ ማንነት፣ ፍላጐት፣ ማህበራዊ ኑሮ የሚሉት ነገር እንዳለ ያነሳ ሲሆን ጥናቱ ካነሳው አላማ አንፃር በተወሰነ መልኩ ግቡን መትቷል። ይህ ማለት በተሰበሰቡ ግጥሞች ውስጥ የማህበረሰቡን ማንነትና የኑሮ ሁኔታ የሚያንፀባርቁ የተኸላይ ሀሳቦችን የያዘ ነው።

"በደምበጫ አካባቢ የሚገጠሙ የውቂያ ግጥሞች ስነቃላዊ ባህርያት"/1993/ ሞላ ፈለቀ ያቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ነው። የሞላጥናት የውቂያ መሳሪያዎች፣ የውቂያ ስነ ስርዐት፣ የውቂያ ግጥም ስነ ቃላልዊ ባህሪ፣ የውቂያ ግጥሞች ከቃላዊነታቸው፣ ከክዋኔያቸው እና ከመከሰቻቸው አንፃር ተመልክቷል። የሞላ ትንተና ያተኮረባቸው ግጥሞች የበሬን አስፈላጊነት የሚያሳይ፣ ብሶትን የሚያንፀባርቁ፣ ተስፋን የሚገልፅ በማለት ከፋፍሏቸዋል።

ሞላ በጥናቱ ውስጥ የውቂያ መሳሪያዎችን እና የውቂያ ስነ ስርዐትን በጥናቱ አካቷል። በዚህ ምክንያት ስለግጥሞቹ ይዘት ብቻ ሳይሆን ስለመገልገያ መሳሪያዎች ይገልፃል። ይህ በጥናቱ የሚታይ ጠንካራ ጐን ነው። የሞላ ጥናት አላማው ስነቃልን ሰብስቦ ማስቀመጥና ከስነ ቃል አንፃር መገምገም ነው። ጥናቱ ከአላማው አንፃር የማህበረሰቡ ሀብት የሆነውን የውቂያ ላይ ስነ ቃልን በተወሰነ መልኩ ሰብሰቦ ማስቀመጡ ግቡን መትቷል ለማለት ያስችላል።

ሚሊዮን ስዩም "የገበሬውን ሙያና ኑሮ የሚያንፀባርቁ የአማርኛ ግጥሞች" /1973/ በሚል ርዕስ ጥናቱን አቅርቧል። በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ የአፋዊ ኪነተ ቃል

ባህርያ የስራ ዘፈኖች ይዘታዊ ትንተና፣ ስለ እርሻ ዘፈኖች ግጥም እርሻ፣ ውቂያ፣ በሬ፣ ገበሬና የገጠሪቱ ሴት እንዲሁም የገበሬውን መጨቆን የሚያሳዩ ግጥሞች ከነትንታኔያቸው አቅርቧል፡፡

ሚሊዮን ስለአፋዊ ከነተቃል ባህሪ ከገለፀ በኋላ በአፋዊ ኪነተቃልና በግብርና መካከል ያለውን አጠቃላይ ዝምድና ለማሳየት ሞክሯል፡፡ በዚህ ውስጥ ስለ አፋዊ ኪነተ ቃል ሲገልፀ "ከእረኛው ጀምሮ እስከ ገበሬው አፋዊ ኪነተቃል አብሮ የሚኖር የተለያዮ ስሜቶች መግለጫ፣ የስራ ደስታ ሀይል ነው" ይላል፡፡ የስራ ዘፈኖች በሚው ንዑስ ርዕስ ስር ሩዝሬኒጋንን በዋቢነት በመጥቀስ ምንነታቸውን ይገልፃል፡፡

ሚሊዩን ከተነሳበት አላማ አኳያ ሲታይ መሉበሙሉ ሥራው ግብ መች አይደለም፡፡ ምክንያቱም አላማው የገበሬውን ሙያ ማሳየት ስለሆነ በጥናቱ ውስጥ የገበሬውን ሙያ ሙሉ በሙሉ የሚያይ ጥናት አልተሰራም፡፡ የሚሊዮን ጥናት የገበሬውን ሙያ ከማሳየት አንፃር ሲታይ የተሰበሰቡት ግጥሞች በጣም ትንሽ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ገበሬን የሚገልፁ ግጥሞች እነዚህ ብቻ አይደሉም፡፡ እንደ ርዕስ ጉዳዩ ሰፋት የተሰበሰቡና የተተነተኑ ግጥሞች ትንሽ መሆናቸውን የጥናቱ ድክመት ነው፡፡

ባዩ መኩሪያ "በደብረ ማርቆስ አውራጃ የገበሬን ስራ እንቅስቃሴ የሚያንፃባርቁ ባህላዊ ግጥሞች ይዘት ትንተና" /1976/ በሚል ርዕስ ጥናቱን አቅርቧል፡፡ ባዩ የስራ ግጥሞች ምንነትና ከስራው ጋር ያላቸውን ተራክቦ፣ የስራ ግጥምን በየስራ ዘርፎች በመከፋፈል ይዘታዊ ትንታኔ መስጠት እና የግጥሞችን ስብስብ ያጠቃልላል፡፡ የስራ ግጥሞች ከስራው ጋር ያላቸውን ተራክቦ ሲገልፅ ስነ ቃል ከህዝብ ባህል አንዱ ዘርፍ መሆኑንና ከተፃፋ ነገሮች የሚለዩበት ባህርያት፣ ክዋኔ፣ ተደራሲና አጋጣሚ መሆናቸውን ፊቃደ አዘዘንና ሩዝሬኒጋንን በመጥቀስ ገለጿል፡፡ ባዩ በስራው ውስጥ የስራው ትኩረት የሆነው የስነቃል ምንነት የገለፀ መሆኑ ጥሩ ጐን ሲሆን ግቡ ከአላማው አንፃር ሲታይ ገበሬዎች በስራ ላይ ያላቸውን እንቅስቃሴ የሚገልፁ ግጥሞች መሰብሰባቸው በተወሰነ መልኩ ግብ መች ሆኗል፡፡

ከላይ ያየናቸው የበሺር ፈለቀ "የጊምባ እርኞች የሚያስማቸው ግጥሞች" የሚለው ጥናት እና የተኸላይ ትዕዛዙ ጥናት "የአክሱምና አካባቢዋ እረኞች የሚያስሟቸው የዘፈን ግጥሞች" ከሚሉት ጥናቶች ጋር የሚመሳሰለትና የሚለያዩበት መንገድ አለ፡፡ ይኸውም ይህ ጥናት ከበሺርና ከተኸላይ ጥናት ጋር የሚዛመደው ሁሉም በእረኛ ግጥሞች ላይ ተመስርተው የይዘት ትንተና ላይ ያተኮሩ መሆናቸው ሲሆን የሚለያዩበት ደግሞ

የበሺርና የተኽላይ ጥናቶች የግጥሞችን ቅርፅ የሚመለከቱ መሆናቸው እንዲሁም ጥናቱ የተመሰረተበት ማህበረሰብ፣ እና በእነሱ ጥናቶች ውስጥ ግጥሞቹ በሚዜሙባቸው የስራ አይነቶች መሰረት የተከፋፈሉ መሆናቸውነው፡፡ የተኽላይ ጥናት ከዚህ ጥናት እና ከበሺር ጥናት የሚለዩበት መንገድ አለ፡፡ ይኸውም ጥናቱ የተመሰረተበት አካባቢ ያለው የህብረተሰብና የቋንቋ ልዩነት ነው፡፡

ይህ ጥናት ከላይ ከተጠቀሱት ጥናታዊ ጽሑፎች ማለትም የሞላ ፈለቀ “በደምበጫ አካባቢ የሚሰሙ የውቂያ ግጥሞች ስነቃላዊ ባህርያትና ይዘት” 1993 እንዲሁም ባዩ መኩሪያ “በደብረማርቆስ አውራጃ የገበሬውን የስራ እንቅስቃሴ የሚንፀባርቁ ባህላዊ ግጥሞች ይዘት ትንተና እና ሚለዩን ስዮም “የገበሬውን ሙያና ኑሮ የሚያንፀባርቁ ባህላዊ ግጥሞች ይዘት ትንተና ከሚሉት ጥናቶች ጋር የሚዛመዱበትና የሚለያዩበት መንገድ አለ፡፡

እነዚህ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉት ሁሉም ጥናቶች ስነ ቃል ላይ በመመሰረት ግጥሞች የስራ ግጥሞች ላይ ያተኮሩ መሆናቸው ነው፡፡ እነዚህ ስራዎች ከዚህ ጥናት የሚለዩት ደግሞ ሁሉም ጥናቶች የስራ ግንጥሞች ላይ ያተኮሩ መሆናቸው፣ ጥናቱ የተመሰረተበት አካባቢ የተለየ መሆኑ እንዲሁም ይህ ጥናት የእረኛ ግጥሞች ላይ የተመሰረተ መሆኑ ከሌሎች የሚለይበት መንገድ ነው፡፡

የሚሊዮን ስራ ከሌሎች የሚለይበት አንድ መንገድ አለ ይህም ሚሊዮን አካባቢ ሳይለይ ከተለየዩ የአገሪቱ ክፍሎች በተሰበሰቡ የአማርኛ የስራ ግጥሞች ላይ የሚያተኩር መሆኑ ከሁሉም ይለየዋል፡፡

### ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

## 2.2. የቃል ግጥም ምንነት

ቃላዊ ግጥም ከትውል ወደ ትውልድ የሚተላለፍ በቃል የሚባል፣ የሚዜም፣ የሚገጠም ነው፡፡ ቃላዊ ግጥም ብዕርና ወረቀት ሳይሰፍር በማህበረሰቡ ዘንድ በቃል ሲከወን የቆየ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ሩዝ ፊኒጋን እንደሚከተለው ገልፃለች፡፡ “ቃላዊ ግጥም በቃል የሚተላለፍ ነው፡፡ በጽሑፍ ከዋለ ስነ ግጥም ጋር ስናነፃፅረው ስርጭቱም ሆነ ክዋኔው በህትመት ላይ የሰፈረ ሳይሆን በቃል የሚባል ነው፡፡” (1977፡16)

ቃል ግጥም ከፈጣሪ (ደርዳሪ) ወደታዳሚ በቃል የሚተላለፍ ነው፡፡ ፈቃደ አዘዘ አፋዊ ኪነተቃል በማለት እንደሚከተለው ገልፆታል፡፡

“አፋዊ ኪነተቃል በአደራረሱ፣ አከዋውኑ፣ ተስተላልፎውና አቀራረቡ ብዙ ጊዜ በቃልና በመዜም የሆነ፣ በዘፈን፣ በሙሾ፣ በእንጉርጉሮ በሌሎችም ተመሳሳይ ዜማዊ ቅርፆች ውስጥ የሚገኝ ህዝባዊ ግጥም ነው፡፡(1991፡84)

ቃል ግጥም በስነቃልነት አንድ ህዝብ ባህሉን፣ ወጉንና ስርዓቱን፣ ውስጣዊ ስሜቱን ከአንድ ትውልድ በቃል ለማስተላለፍ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡ ቃል ግጥም በቃል እየተከወነ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ቆይቷል፡፡ ባልተማረው የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ የቃል ግጥም ጐልቶ የሚታይ በመሆኑ በገጠሬው ነዋሪ በደቦ ስራ፣ በአረኞች፣ በለቅሶ፣ በሰርግ፣ በእርሻ፣ በየአመት በአሉ ውበትና ለዛ ባለሙ መልኩ በማዜም ይጠቀሙበታል፡፡

ቃል ግጥም ሰው በአምዕምሮው የሚያመላልሰውን ሀሳብ የሚያመጣበት መንገድ ነው፡፡ በቃል ግጥም ሀሳብን ለማስተላለፍ የተማረ፣ ያልተማረ፣ ልጅ አዋቂ የሚል ውሳኔ የለም፡፡ የሰው ልጅ ሀሳቡን ለሌሎች በቃል ማስተላለፍ የዕለት ተዕለት ኑሮ ማለት ስለሆነ ዘወትር ከሰው ልጅ የማይነጠል ሂደት ነው፡፡

በአጠቃላይ የቃል ግጥም በቃል ከሚተላለፉ ነገሮች አንዱ ሲሆን ትዝታን፣ ፍቅርን፣ ሐዘንን፣ ትዝብትን፣ ማጣጣል፣ ልመናን፣ ክፋትን ደግነትና ሌሎችንም ሁኔታዎች በሽለላ፣ በዘፈን፣ በእንጉርጉሮ ወዘተ መልክ በማቅረብ መልዕክትን ማስተላለፊያ መንገድ ነው፡፡

## 2.3. የቃል ግጥም አከዋወን

የሰው ልጅ ያሳለፋቸውን የህይወት ገጠመኞች በጽሑፍ አልያም ቃልን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር አዋህዶ ለሌሎች ያቀርባል፡፡ ከእነዚህ ሁለት መገለጫ መንገዶች መካከል ቃል ግጥሙን ሙሉበሆነ መንገድ ለሌሎች የሚገልፀው በክዋኔ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ፈቃደ አዘዘ እንደሚከተለው ይገልፃል፡፡

“ቃላዊ ግጥም ህይወቱ በክዋኔ መሆኑን ክዋኔውም ምልዑነት የሚያገኘው አንድም ገላጭ አካላዊ እንቅስቃሴዎች ወይም ቃላት ዜማና አካላዊ እንቅሰቅሴዎች ሲገኙ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡”(1970፡80)

ክዋኔ አንድን ረቂቅ ነገር አጉልቶ ለማሳየት ነው፡፡ ግጥም በህዝብ መካከል ካልተከወነ ህልውናውን አጣ ማለት ነው፡፡ ክዋኔ በሚደረግበት ጊዜ ቃላዊ በመሆኑ የግድ

ተደራስያንና ደራሲያን ግንባር ለግንባር መገናኘት አለባቸው፡፡ ሩዝፊኒጋን ይህን ጉዳይ አስመልክታ የገለፀችው እንደሚከተለው ነው፡፡

"... የስነቃል ክዋኔ ከተደራሲያኑ ነጋር ፊት ለፊት ከመገናኘት የሚያመልጥበት መንገድ የለም፡፡"(1970፡10)

ቃል ግጥም በሚከወንበት ጊዜ ከዋኙ በአቀራረቡ ነፍስ ይዘራበታል ግጥሙን አውራጁ ማራኪ፣ አስቂኝ፣ አሳዛኝ፣ ወዘተ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ግጥም እንደየ ሁኔታው ድምፅን በማቅጠን፣ በማወፈር፣ በማጉርነን፣ የብስጭት ድምፀት የትዕግስት ድምፀት፣ ወዘተ በመጨመር መናገር የበለጠ ማራኪነት እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡ ከዋኙ በሰርግ ቤት፣ በለቅሶ ቤት፣ በስራ ቦታ፣ ታቦት ሲወጣና ሲገባ በአዲስ አመት መጀመሪያ የተለያዩ የቀልድ ግጥሞች እንዳሉት ሁሉ የአከዋወን ዘይቤም የተለያየ ነው፡፡ ከዋኙ በራሱ ሰዐት መሆን የፈለገውን ባህሪ ተላብሶ ሐሳቡን ሲያስተላልፍ ሆን ብሎ ተዘጋጅቶ፣ ብዙ ጊዜ አስቦበት የቀረበ እንጂ በአለበት ቅፅበት ብቻ ተቀነባብሮ የሚቀርብ አይመስልም፡፡

ቃል ግጥም ህልውና የሚኖረው ከላይ እንደተገለፀው አቅራቢው ወደ ከዋኙ ሁኔታዎችን ከራሱ ህይወት ጋር አጣጥሞ ውበት የተላበሰ አድርጎ ሲያቀርብ ነው፡፡ ይህም ማለት የቃል ግጥሞች ከዘፈን፣ ከፋከራ፣ ከሙሾ፣ ከእንጉርጉሮ፣ በአጠቃላይ ከሚከወኑ ዜማዊ ውበታቸውን፣ ጣዕማቸውን፣ ለዛቸውን፣ አስደሳችነታቼውን፣ አሳዛኝነታቸው፣ እንደጠበቀ የሚገኙት ከዋኝያቸው ሲሰምር ነው፡፡

ክዋኔ በተለያየ አጋጣሚ የሚደረግ ስርዐት ነው፡፡ በበዓላት የሚዘፈኑ ዘፈኖች፣ በለቅሶና በሰርግ ስርዓት ላይ የሚገጠሙ ግጥሞች እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ክዋኔ አንድ ማህበረሰባዊ አጋጣሚ ወይም የመሰብሰቢያ ምክንያት በተሳታፊዎች ፊት የሚነገር፣ የሚዜምና በድርጊት የሚቀርብ እንጅ እንደ ጽሑፋዊ ስነጽሑፍ በአንድ ደራሲ ተደርሶ በወረቀት ሰፍሮ ለብቻው የሚነበብ አይደለም፡፡ /ዘሪሁን 1998፡22/

በአጠቃላይ ቃላዊ ግጥም ስሜት ቀስቃሽ የሚሆነው መልዕክቱ ግብ መች ሆኖ የሚገኘው የክዋኔ አካላት በሙሉ ሲቀርቡ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የእረኛ ግጥም ይዘት ትንተና

### 3.1. የእረኞች ምንነት

እረኞች ውሏቸው ከከብቶች ጋር ነው። አንዳንዶቹ ተቀጥረው ከተለያየ አካባቢ በመምጣት በሰው ቤት የሚሰሩ ናቸው። እነዚህ እረኞች የራሳቸውን ከብቶች ወይም ተቀጥረው የሚሰሩበትን ቤት ከብቶች ይጠብቃሉ። የእረኛ ስራ ይህ ብቻ አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ሰብል ጥበቃ፣ ሰብል በደረሰ ጊዜ አጨዳ፣ ውቂያ፣ በራይ የመሳሰሉትን ስራዎች ይሰራሉ። ነገር ግን ይህ ተጨማሪ ስራ ቢሆንም በዋናነት የሚሰሩት ከብቶችን መንከባከብና ማገድ ነው።

በክረምት ጊዜ አብዛኛው መሬት በቡቃያ ይሸፈናል። በዚህ ጊዜ በአካባቢው ባሉት መንደሮች ሁሉ የከብት ማሰማሪያ ይጠፋል። በዚህ ምክንያት ብዙ ጊዜ በክረምት የአካባቢው ከብት ሜዳ ይውላል። በበጋ ሜዳ አይውልም ማለት አይደለም። ብዙ ጊዜ በበጋ መሬቱ በሰብል ስለሚሸፈን አንዳንድ አካባቢዎች ከብቶች በሰብሉ መሬት ሲበሉ ይውላሉ።

በክረምት ወቅት አካባቢው ቀዝቃዛ ከመሆኑ የተነሳ እረኞች የሚለብሱት ማቅ፣ ድሪቶ፣ ከበግ ቆዳ የሚሰራ በአካባቢው ሲጠራ ደበሎ ጉጃም አዘነ የመሳሰሉትን ቅዝቃዜውን ለመከላከል ይለብሳሉ። ዝናብ በመጣ ጊዜ ሊያድናቸው የሚችል ከቄጤማ የተሰራ ገሳ፣ እንዲሁም ጃንጥላ ይለብሳሉ። እያንዳንዱ እረኛ ከብቶችን ሲያግድ ከገሳ ወይም ከባህር ዛፍ ቅርፊት የተገመደ ጅራፍ ይኖረዋል። የጅራፉ ጫፍ በፈረስ ጭራ የተገመደ ነው። ይህ ጅራፍ ከብቶች በሚሄዱበት ጊዜ ሲያጮህ ከብቶቹ በሩጫ እንዲመለሱ ይረዳዋል። ከዚህ በተጨማሪ የጅራፍ ማጮህ ውድድር እያንዳንዱ እረኛ ይጫወትበታል።

በዚህ አካባቢ ያሉ እረኞች ህብረታቸውን የሚጠናክሩበት በጉርብትና የተቀራረቡ ሲሆኑ ነው። በአንድ አካባቢ በእረኝነት ስራ ላይ ከዕለት ወደ ዕለት የሚገኛኙ ከሆነ የመተሳሰባቸው ሁኔታ የበለጠ ይሆናል። እነዚህ እረኞች በህብረት ሆነው በሚውሉበት ጊዜ ከጨዋታ አልፈው አንዳንድ ስራዎችን ይሰራሉ። ገመድ መግመድ ቅርጫት መስራት የመሳሰሉትን ሥራዎች በህብረት ይሰራሉ።

በክረምት ጊዜ እረኝነት ከበጋው የበለጠ ጥንካሬ ይጠይቃል። በዚህ ጊዜ አካባቢው በማሳ የተሸፈነ በመሆኑ ከብቶችን መጠበቅ እረፍት አይሰጥም፣ አካባቢው በጉም ስለሚሸፈን በጐች ወይም ከብቶች በሌባ እንዳይሰረቁና ወደ ሌላ ቦታ ሄደው እንዳይጠፉ ተግተው

መጠበቅ ይኖርባቸዋል። ስለዚህ እረኞች ለምሳ ወደ ቤት አይመጡም። በበጋ ወራት ግን ይህ ሁሉ ችግር ስለማይኖር እረኞች ከብቶች ሲተኙ በቅርብ ከሚገኘው ከማንም ክምር ወይም አዝመራ ወስደው ይበላሉ። በክረምት ወቅት ግን በሚውሉበት ሜዳ እንጀራ፣ ዳቦ ወይም ቆሎ ይዘው ይሄዳሉ።

እረኞች ከብቶችን በሃላፊነት ከመጠበቅ አልፎ አብረው በሚውሉበት ጊዜ የራሳቸው የሆነ እንዲሁም ከማህበረሰቡ የሰሙትን፣ ያዩትን በሜዳ ላይ ይጫወቱታል። ከእነዚህ ጨዋታዎች ውስጥ ዘፈኖች፣ ቀልዶች፣ ተረቶች፣ ገና ጨዋታ፣ ገመድ መዝለል፣ ውሃ መራጨት የመሳሰሉት ይገኙበታል።

በመሆኑም በጨዋታው ላይም ሆነ ያለጨዋታ በእረኞች የሚደረደሩና የሚዘፈኑ ግጥሞች ሰፊ ማህበራዊ ጉዳዮችን ይዳስሳሉ። በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ያሉሰዎች በግጥም የሚያስተላልፉትን መልዕክት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማህበራዊ ጉዳይን ይዳስሳሉ። በዚህ ጥናትም በአንድ የግጥም ርዕስ ስር የሚገኙ ግጥሞች ከአንድ በላይ የሆኑ ጉዳዮችን ያነሳሉ። ስለዚህ ግጥሞቹ በዋናነት የሚዳስሷቸውን ማህበራዊ ጉዳዮች ከተሰበሰቡት ግጥሞች ውስጥ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

## 3.2. የጅራፍ ግጥሞች

የጅራፍ ጩኸት በእረኞች ዘንድ የሚዘወተር የጨዋታ አይት ነው። እረኞች በአንድ አካባቢ አብረው ሲውሉ የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ። ከብቶችን ሜዳ ላይ በማሰማራት ጅራፍ ይዘው በማንጓት ይወዳደራሉ። አንደኛው ወገን ሌላኛውን ወገን ከአንተ ጅራፍ የእኔ ጅራፍ ጩኸት ይበልጣል በማለት እያንዳንዱ የራሱን ከፍ የሌላውን ዝቅ ያደርገዋል። ሆኖም እረኞች በጅራፍ ጩኸት ውድድር ጊዜ ያሸነፈው ቡድን ይዘፍናል። ተሸነፈውም ቢሆን ራሱን ለማጠናከርና ለማበረታታት የራሱን የመልስ ዘፈን ይዘፍናል። ይህን የጅራፍ ውድድር ሁለትና ከዚያ በላይ ሆነው ይጫወቱታል። እነዚህ ተጫዋቾች እንደሚከተለው በመቀባበል ይዘፍናሉ።

ሀ. የአንተ ጅራፍ ለከስካሳ
የኔ ጅራፍ አንበሳ
ስማው ስማው ሲያገሳ።

ለ. የአንተ ጅራፍ ስትቆረጥ
በኔ ለመድረስ ወገብህ አይቆረጥ።

ሁለት እረኞች አንድ በሰው ቤት እየተቀጠረ ሰርቶ የሚበላም ሆነ በወላጆቹ ቤት እንደልቡ የሚኖር በአንድ ሜዳ ከብት ሲያግዱ የሚጫወቱት ጨዋታ አለ፡፡ ብዙ ጊዜ እነዚህ እረኞች የሚጫወቱት ምሽት አካባቢ ከብቶችን ወደ መንደር አስጠግተው ቆይተው ወደ በረት እስኪያስገቡ ሩቅና ሩቅ ሆነው ኮረብታ ላይ በመቆም ጅራፍ እያጮኹ የሚተራረቡት ድርድር ነው፡፡ ወቅቱ የክረምት ወራት እየተገባደ መጥቶ የደብረታቦርን ወይም የቡሄን በዓል በመንተራስ ነው ጨዋታውን የሚያዘወተሩት፡፡

በአካባቢው ውስጥ ያሉ ሰዎች ከብቶችን የሚያግዱላቸው ልጆቻቸው ብቻ አይደሉም፡፡ ከብት የሚያግድ ሰው ይቀጥራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሌም ከአሰሪዎች ቤት የማይለምድ በየሰዎች ቤት እየዞረ የሚቀጠርን እረኛ እንዲሁም በእናት እና በአባቱ ቤት ያለ እረኛ ከብቶቹን አይቆጣጠርም ሁሌም ቤት ውስጥ ይውላል በማለት ሚያውቁት አረኞች እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

ሀ. ንሳ ተቀበል  የጅራፌን መልዕክት
   መሰከረም  ጠባ ስትዞርለከት
   ብታስታውሰው  አበቧ ልሙጀ
   እንግዲህ ይብቃህ  ያለው ምድጃ

ለ. ንሳ ተቀበል የጅራፌን  ጩኸት
   ቡሃቃውን አምጣ ከትሿ ማጀት
   ታች ምድጃ ስጣት ለናትህ
   ስታነኳኩር እንድታጉስህ፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን ግጥም በተለያዩ አካባቢዎች እረኞች ይዘፍኑታል፡፡ ግጥሙ ከላይ ከያዘው ሃሳብ በተጨማሪ ደረቁ በሚባለው ቀበሌ ውስጥ ያለው የሚባል እረኛ አለ፡፡ያለው በጧት የማይነሳ ሰነፍ፣ እንቅልፋም ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በአካባቢው ያሉ የጓደኞቹ ከብቶች በጠዋት ወጥተው ሲበሉ የያለው ከብቶች ፀሐይ እስኪወጣ ድረስ ከቤት አይወጡም፡፡ በሰው ቤት ተቀጥሮ ቢሰራም ስንፍናው ቀጣሪዎችን አስቸግሯል፡፡ ይህ ባህሪው በጓደኞቹ ዘንድ የሚታወቅበት ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም በአካባቢው ውስጥ በሚገኙ ቤቶች ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ቤት በመቀያየር ይታወቃል፡፡ በዚህም ምክንያት  በዚህ ምክንያት የያለው ጓደኞች ስንፍናውን፣  ከአንዱ ቤት ሌላ ቤት የሚሄድ መሆኑን በጅራፍ ውድድር ጨዋታቸው ላይ ይገልፁለታል፡፡

## 3.3. የስድብ ግጥሞች

የስድብ ግጥሞች በሰዎች ላይ ያየነውን ባህሪ የአካል እንቅስቃሴ ወይም ሌላ ነገር መንቀፍ፣ በንግግር ማዋረድ፣ ማነወር ማለት ነው፡፡ የስድብ ግጥሞች አንድ ሰው የሰራው ስራ ትክክል እንዳልሆነ ለማሳየትና ለመገሰጽ የሚቋጠሩስንኞች ናቸው፡፡ የስድብ ግጥሞች በአደባባይ በግልጽ ለመናገር ተናጋሪና አድማጭ ባሉበት የሚባሉ / የሚከሆኑ/ ናቸው፡፡

ስድብ ማህበረሰቡን ለማስተማር፣ ከስህተቱ ለማረም፣ ከጥፋቱ ለመጠበቅ፣ ለደስታና ለመጫዋታም ሲባል የሚደረጉ ግጥሞችን የያዘ ነው፡፡ ህብረተሰቡ ስለራሱ፣ ስለባህሉ፣ ስለተፈጥሮው፣ ስለፍላጐቱ፣ስለማህበራዊና ግላዊ ችግሩ እንዲሁም ስለሌሎች ነገሮች ያለውን አመለካከት በግልጽ እንዲናገርና እንዲያስረዳው በማድረግ ረገድ ሊያሳድሩ ከሚችሉት አዎንታዊ ተፅዕኖ አንፃር ሊታዩ ይገባቸዋል፡፡

የስድብ ግጥሞች የተለያዩ መከሰቻዎች አሏቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል የአህያ መጣች ግጥም፣ የእንካ ስላንትያ ግጥም፣ እንዲሁም በልዩ ልዩ ቅርፆች የተገጠሙ ሌሎች ግጥሞችም ይገኙበታል፡፡

### 3.3.1. የአህያ መጣች ግጥሞች

ይህ የግጥም ቅርፅ መቼ እንደተጀመረ ባይታወቅም በደጋዳሞት አካባቢ ያሉ እረኞች በብዛትም ባይሆን ሲጠቀሙበት ይስተዋላል፡፡ እረኞቹ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ "አው አው" ብለው ጉሮሮአቸውን ከጠራረጉ በኋላ ግጥሙን ያሰማሉ፡፡ እነዚህ ግጥሞች የተለያዩ አሉታዊ ድርጊቶችን የሚነቅፋ፣ የሚያወግዙ፣ እንዳንዴም ለማስጠንቀቅ የሚሞክሩ ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡-

አህያ መጣች ተጭና ወንበር
እጣን አሮጌው ይቀጠፍ ጀመር፡፡

ይህግጥም የሚያሳየን በሽታ በአካባቢው ውስጥ መኖሩን ነው፡፡ በሽታ በአንድ አካባቢ ካለ ሁሉም አካባቢ በተለያየ መንገድ መድረሱ አይቀርም፡፡ እረኞች የመጣውን /የገባውን/ በሽታ ከሰሙ በአህያ መጣ ግጥማቸው እንደ ማስተጠንቀቂያ በመቁጠር ያዜሙታል፡፡

አህያ መጣች በተባለው ግጥም አያሌ የሆኑ ማህበራዊ ጉዳዮች ይነሳሉ፡፡ የአካባቢው ህብረተሰብ ፍላጐትና ምኞች ይንፀባረቅበታል፡፡ ከዚህ የተነሳ እረኞች የግል ይዞታ የነበረው የወላጆቻቸውን መሬት በክልል ወደ አምራች ይዞታ ወይም ያመርታል ወደ ተባለ ሰው ሲዞር የተቃውሞ ድምጽ በግጥማቸው ያሰማሉ፡፡ እረኞች ይህን ድርጊት የፈፀመውን ዳኛ ወይም

የአካባቢው ሊቀመንበር ከብት ጥበቃ ቦታ ተሰባስበው በሚጫወቱበት ወቅት እንዲህ እያሉ ይሰድቡታል፡፡

አህያ መጣች ተጭና ገብስ
ምን የሚሉት ነው መሬት ማውረስ፡፡

በአካባቢው ውስጥ ካሉ እረኞች አንዳንዶቹ ከተወለዱበት አካባቢ ርቀው በመምጣት በሰው ቤት የተቀጠሩ ናቸው፡፡ እነዚህ እረኞች የኑሮአቸውን ሁኔታ በሰው ቤት የሚንከራተቱት፣ በተጕሳቆለ ኑሮ ያሉ፣ የሚራቡ፣ የሚንጠራወዙ/የሚገፉ/ ሆነው ግን የተለያየ ባህር ያላቸው ሊሆን ይችላል፡፡ አንደኛው ሆዳም፣ ሌላኛው ሌባ፣ እንዲሁም ሰነፍና ራሱን ንፅህና የማይጠብቅ ይኖራል፡፡ በዚህ ጊዜ እረኞች በአህያ መጣች ግጥም እየተቀባበሉ እንደሚከተለው ይሰዳደባሉ፡፡

ሀ. አህያ መጣች ተጭና ኩታ
ያንደኛየ ሆዱ ገበታ፡፡

ለ. አህያ መጣች ተጭና ለምድ ያ ኳደኛየ ማዞርያ ሆድ፡፡

ሐ. አህያ መጣች ተጭና ድስት
የእግሩ ቅርጭጭት ያለውብዛት፡፡

ለ. አህያ መጣች ተጭና ጋሻ
ያንደኛየ የመንደር ውሻ፡፡

እረኞች ከብት ሲያግዱ ከመንደር ከማህበረሰቡ ውስጥ ለውስጥ የሚንሾካሽከውን ሚስጥር በሜዳ ያውሉታል፡፡ እነዚህ እረኞች ሁለት ሦስት ሆነው ሲወራ የሚያውቁትን ወይም የሰሙትን በዜማቸው እየተቀባበሉ ይደረድሩታል፡፡ በአካባቢው ውስጥ ብዙ ጊዜ ከባሏ ውጭ ሌላ ወንድ ጋር ግንኙነት የምታደርግ ሴት የተጠላች ትሆናለች፡፡ ይች ሴት ብዙ ጊዜ የባሏን ቤት ትታ ውሽማዋን ወደ ምታገኝበት ቦታ ስትሄድ ከታየች በእረኞችም በሌሎችም ሰዎች ትሰደባለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሚስቱ ከሌላ ወንድ ጋር ግንኙነት አላት ተብላ የምትታሰብ ሴት ባል በማህበረሰቡ ዘንድ የተናቀ ነው፡፡ በሌሎች ዘንድ ክብርን ያጣል፡፡ ምክንያቱም ሚስቱን መቆጣጠር አይችልም ተብሎ ይታሰባል፡፡ እነዚህን ሰዎች ለማንቋሸሽ ከቤተሰቦቻቸው ወይም በመንደር ሲወራ የሰሙትን እረኞቹ በከብት ጥበቃ ላይ እንዲህ ብለው ይሰድቧቸዋል፡፡

ሀ. አህያ መጣች ተጭና ዳባ
እገሊት ሄደች ጉድባ ለጉድባ፡፡

ለ. አንተ አያ እገሌ  የእንትና ባል
ምሽትህን ጠብቅ አትበል ቸል።
እንዲህ ተሆነ የባልስራቱ
ቶሎ ቶሎ በል ይቅረብ እራቱ።
እግሯንም አጥበህ አደስ ቀብተህ
ላክለት እንጅ ላያ ውሽሜ
ለሜዳ አህያ ለያሽምሽሜ።

የአካባቢው እረኞች በአካባቢው ህብረተሰብ ውስጥ ሌብነት የተጠላ ስነ ምግባር መሆኑን ያውቃሉ። በአካባቢው ውስጥ ብዙ ሌቦች አሉ። እነዚህ ሌቦች በግ፣ ፍየል፣ በሬ፣ አልፈውም የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ጨለማን ተገን በማድረግ ይሰርቃሉ። ከእነዚህ ውስጥ በአካባቢው ታዋቂ የሆነው እና ብዙ ጊዜ ፍርድ ቤት የሚቀርብ ሌባ አንዷለም ነው። አንዷለም በዚህ ስራው  ማህበረሰቡ የሚፈራው አስቸጋሪ ሰው ነው። ሆኖም ይህ ስራው ከማህበረሰቡ አልፎ በእረኞች ዘንድ እንዲታወቅ አድርጎታል። በዚህ ምክንያት ቤተሰቦቻቸው በሌቦቹ  ሲማረሩ/ ሲያዝኑ/ የሰሙት እረኞች በጨለማ ሊሰርቅ የሚመጣውን አንዷለምን በድንጋዬች መመታቱን፣ ጉድጓዶች ውስጥ መግባቱን ሰምተው አንዷለምን ሲያዩ እንደሚከተለው ይሰድቡታል።

አህያ መጣች ተጭና ሙሬ
ከጉድጓድ ገባ ሲሰርቅ በሬ።

## 3.3.2. የእንካ ስላንትያ ግጥሞች

በአካባቢው ውስጥ ያሉ እረኞች የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ። ከእነዚህ ጨዋታዎች አንዱ ግጥሞች እየገጠሙ እርስ በርስ እየተቀባበሉ የተለዩ ጉዳዮችን የሚያነሱበት የእንካ ስላንትያ ግጥም ነው። በዚህ ግጥም የተለያዩ ጉዳዮች ይነሳሉ። ጨዋታው አቀባይና ተቀባይ ወይም ጠያቂና ተጠያቂ ባሉበት ይከወናል። እረኞች ይህንን ጨዋታ ሲጫወቱ በስምምነት ስለሆነ አያጣሉም። ጨዋታው ፀያፍ ስድብ ላይ የተመሰረተ ተራ አርቲቡርቲ ስድብ ነው።

እረኞች ብዙ ጊዜ ከተለያዩ የልብስ ቁርጥራጮች የተስፋሱሪ ወይም ኮት ይለብሳሉ። ይህ ልብስ ለእንቁጣጣሽ ካልሆነ አይታጠብም። በዚህ ምክንያት ብዙዎቹ ልብሳቸው ቅማልና

ቁንጫ የያዘ ነው፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ መካከል የበለጠ ቅማልና ቁንጫ የሚታይበት ልጅ በጓደኞቹ እንደሚከተለው ይሰዳደባሉ፡፡

| | |
|---|---|
| ጠያቂ | እንካስላንትያ |
| ተጠያቂ | በምንትያ |
| ጠያቂ | በቆርበት |
| ተጠያቂ | ምናለ በቆርበት |
| ጠያቂ | ጉንጭህ ተወጥሯል ቅማል የሞላበት፡፡ |

እረኞች ከላይ እንደተገለፀው በእንካ ስላንትያ የተለየዩ ጉዳዬችን ያነሳሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ እረኞች ከአንድ ሰፈር የሚሰባሰቡ ስለሆነ የአንዱን ቤት ሚስጥር ሌላኛው የማወቅ ዕድሉ አላቸው፡፡ ሆኖም አንዱ እረኛ የሌላውን እረኛ እናት ስንፍና፣ ንፁህናዋን የማትጠብቅ ወይም እራሷን የማትቆጣጠር ከሆነች ከእርሷ አልፎ ልጆችንና ባሏን ታሰድባለች፡፡ ከዚህም የተነሳ ይህንን ድርጊት የምታደርግ ሴት ልጅ በእረኞቹ መካከል ከተገኙ እረኞች እርስ በእርስ እየተቀባበሉ እንደሚከተለው ይሰድቡታል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. | ጠያቂ | እንካ ስላንትያ |
| | ተጠያቂ | በምንትያ |
| | ጠያቂ | በደንደሮ |
| | ተጠያቂ | ምናለ በደንደሮ |
| | ጠያቂ | እናትክን በዳልህ አይጡ ተንደርድሮ፡፡ |
| ለ. | ጠያቂ | እንካ ስላንትያ |
| | ተጠያቂ | በምንትያ |
| | ጠያቂ | በሳንቃ |
| | ተጠያቂ | ምናለ በሳንቃ |
| | ጠያቂ | እናትህ ሞተች በእምሷ ፀጉርታንቃ፡፡ |
| ሐ. | ጠያቂ | እንካ ስላንትያ |
| | ተጠያቂ | በምንትያ |
| | ጠያቂ | በቋት |
| | ተጠያቂ | ምናለ በቋት |
| | ጠያቂ | እናትህ ሞተች አሯደርቆባት፡፡ |

እያንዳንዱ ሰው ልጅ ከሌሎች ሰዎች ጋር አብሮ ሲውል መልካምና ጥሩ ስነምግባር ያለው ሊመስል ይችላል፡፡ ነገር ግን እንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ደካማጐን አለው፡፡ ሰው ሆኖ ፍጹም የሆነ ማንም የለም፡፡ እረኞች አብረው ሲውሉ የአንዱን ባህሪ ሌላኛው ያውቃል፡፡ አብረው በሚውሉበት ጊዜ በጨዋታ ጊዜ ሆነ በሌላ ነገር ያላደረጉትን አደረኩ፣ ያላዩትን አየሁ ብለው የሚዋሹ አሉ፡፡ ከቤት ያዩትን ለእርኞች ያወራሉ፣ ከእረኞች የሰሙትን ሳይደብቁ ለቤት ያወራሉ እንደዚህ አይነት ባህር ያላቸው እረኞች በጓደኞቻቸው እንደሚከተለው ይሰደባሉ፡፡

ጠያቂ እንኳ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በጠላ

ተጠያቂ ምናለ በጠላ

ጠያቂ ከጉብሉ ሁላ አንተ ነህ ጠልጣላ፡፡

ጠያቂ እንኳ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በማርዳ

ጠያቂ ከጉብሉ ሁላ አንተነህ ወራዳ፡፡

እረኞች ከተለያየ አካባቢ፣ ቤት እንዲሁም ከተለያየ የዘር ሀረግ የመጡ ሆነው የሚውሉበት የስራ መስክ አንድ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ይህ በመሆኑ አንደኛው ጥቁር፣ ሌላኛው አጭር፣ ደንቆሮ፣ ሌላም የተለያየ የአካል ክፍል አላቸው የሚባሉት በብዛት ቀይ፣ ጠይም፣ ወፍራም እንዲሁም ሁሉንም የአካል ክፍል ያሟሉ ሰዎች ናቸው፡፡ እረኞች ከእነዚህና ሌሎችም የጥሩነት መገለጫዎች አንዱንያጡ እረኞች በመካከል ከተገኙ እንደሚተለው ይሳደባሉ፡፡

ጠያቂ እንኳ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በጌሾ

ተጠያቂ ምናለ በጌሾ

ጠያቄ ከጉብሉ ሁላ አንተነህ ጠቆርሾ፡፡

ጠያቂ እንኳ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

| | |
|---|---|
| ጠያቂ | በድግር |
| ተጠያቂ | ምናለበድግር |
| ጠያቂ | ከጉብሉ ሁላ አንተነህ አንድ እግር። |
| ጠያቂ | እንካ ስላንትያ |
| ተጠያቂ | በምንትያ |
| ጠያቂ | በቁሮ |
| ተጠያቂ | ከጉብሉ ሁላ አንተነህ ደንቆሮ። |

### 3.3.3. ልዩ ልዩ የስድብ ግጥሞች

የሰው ልጅ ባለበት ዘመን ሁሉ አንዱን ከፍ ሲያደርግ አንዱን ሲያንቋሽሽ ማየት የተለመደ ነው። በህብረተሰቡ ውስጥ ያዩትን፣ የሰሙትን ክፋና ደግነገር እረኞች በከብት ጥበቃ ጊዜ እርስ በእርስ የተለያዩ ጉዳዮችን በማንሳት አንዱ አንዱን ከፍ ሲያደርግና፣ ዝቅ ሲያደርግ እናያለን። እነዚህ እረኞች በተለይ ጠዋትና ማታ ከብቶችን በራሳቸው ሳር ውስጥ እየጠበቁ ማዶ ለማዶ በመሆን አንዱ ሌላውን ይሰድበዋል። በሰዎች ላይ የሚታይ ቀጭንነት፣ ወፍራም፣ አጭር፣ ቀይ ወይም ጥቁር የሆነ ሰው እነዚህ ነገሮች ስላሉበት ይሰደባል ወይም ይሞገሳል። ስለዚህ እረኞች አጭር ወይም ቀጭን ኮሳሳ የሆነ ሰው ሲያዩት በመቀባበል እንደሚከተለው ይሰድቡታል።

እከሌ ጉጥር የጉመን አጥር።
ስትሄድ ቅትር ቅትር ስትበላ እንደ ንበጣ
ወዘና የሌለህ ትመስላለህ ቋንጣ።
ባል አገባሁብላ የሽንኩርት እራስ
እሱም በዛ ብሎ ወሰደው ንፋስ።

በአካባቢው ውስጥ ከብት የሚጠብቅ እረኛ እንዲሁም በግና ፍየል የሚጠብቅ እረኛ ማዶ ለማዶ ወይም ጉን ለጉን ሆነው ይጠብቃሉ። የከብቶች እረኛ ከብቶችን በጠዋት አስወጥቶ ካበላቸው በኋላ ሜዳ ሄደው ይተኛሉ። በጐችና ፍየሎች ግን የሚተኙት ለትንሽ ጊዜ ብቻ ነው። በዚህ ጊዜ የክብቶችና የበጐች እረኞች እርስ በርስ ከሚጠብቋቸው እንስሳት የተነሳ የኔ ከብቶች አይረብሹም የአንተ በግና ፍየሎች ይረብሻሉ በማለት ይሰዳደባሉ። የከብት እረኛው ከብቶቹ ሲተኙለትና ቁጭ ሲል እራሱን እያሞገስ የበግና የፍየል ጠባቂውን እንደሚከተለው ይሰድበዋል።

የበጐች እረኛ አመዳም ቅርናታም

የከብቶች እረኛ ውብ አገተ መልካም፡፡

የፍየል እረኛ ፎከቶፎከቶ

የከብቶች እረኛ ሽጋው ተጐልቶ፡፡

ይህ ግጥም የከብቶች እረኛ የኔ ከብቶች አይረብሹም አንተ ከበግና ከፍየል ጋር ስትደክም፣ ስትሮጥ እኔ ቁጭ ብየ እውላለሁ ለማለትና እራሱን ከፍ እያደረገ የበግና የፍየል ጠባቂውን የሚሰድብበት ነው፡፡

ሰዎች በእርጅና ምክንያት፣ በተፈጥሮ ወይም ከወላጅ እንክብካቤ ማነስ የተነሳ በእሳት በመቃጠል ፀጉራቸውን ከግንባራቸው ወይም ከመሃል እራሳቸ የራቀ /የጠፋ/ ይሆናል፡፡ እነዚህ ሰዎች በዚህ ወረዳ ብቻ ሳይሆን በየትኛውም የማህበረሰብ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን በዚህ አካባቢ ያሉ እረኞች በተለያዩ ምክንያቶች ሰዎችን በተመለከቱ ቁጥር በዘፈን መልክ ይሰድቧቸዋል፡፡

| | |
|---|---|
| እኔ ምንቸገረኝ | ጨረቃ ባትወጣ |
| ታበራልኛለች | የእንትና መላጣ፡፡ |

በማንኛውም አካባቢ ከሰዎች የተለየ የሚያደርገው ነገር ያለው ሰው በጥሩም ሆነ በመጥፎ ጐኑ ያዩትን ነገር በተለያየ መንገድ ይገልፁለታል፡፡ እረኞች ከብቶችን በሚጠብቁበት ጊዜ በማህበረሰቡ ውስጥ ያዩትን ነገር ያወጡታል፡፡ ሆኖም ቦርጫም ሰው በመካከላቸው ካለ ወይም የሚያውቁት ሰው ካለ ይሰደባል፡፡ ይህን የሚያደርጉት ቦርጫሙን ሰው በአካባቢው ሲመለከቱት ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ባለቤቱ /ቦርጫሙ/ ሰው በሌለበት ለማንም አይናገሩም፡፡ አንዳንዴ ግን በጣም ቀጭን የሆነ ሰው በአሽሙር ለመስደብ ይጠቀሙበታል፡፡

| | |
|---|---|
| እከሌ ዘጫ | ያኅት መገልበጫ |
| የእኔማ እክሌ | የወገራ በሬ |
| ከሆዱ ላይ ብቆም | ይታያል አገሬ |

እረኞች በብዛት የሚለብሱት ከተለያዩ ጨርቆች የተሰፋ ሱሪ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ባነሳናቸው ግጥሞች እንዳየነው እረኞች ትርፍራፊ ይበላሉ፡፡ እንዲሁም ምግብ ባገኙት አጋጣሚ ሳይመርጡ ይበላሉ፡፡ ይህን ዕድል ያገኘ እረኛ መወፈሩ አይቀሬ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ሜዳ ላይ በሚጫወቱበት ጊዜ ከመካከላቸው አንድ ወፍራም ከተገኘ ከውፍረቱ በተጨማሪ በጨዋታ ጊዜ ልብሱን የሚቀድ ከሆነ በእረኞች እንደሚከተለው ይሰደባል፡፡

የቂጥክን ስባቱን  እውነት አትውደደው

ሱሪህ በተሰፋ  በወሩ ቀደደው፡፡

የሰው ነው ወይ የከብት  እዩት የህንደንደስ

የበላ አይመስለም ወይ አስር አጋሰስ፡፡

## 3.4. የወዘበሬታ/የቀልድ/ ግጥሞች

ወዘመሬታ የሚሰኘው ቀልድ ነው፡፡ ሰዎች በተለያየ ምክንያት በኑሮአቸው ሁኔታም ሊሆን ይችላል  ነገድና ጎሳ፣ ፆታና ስብዕናን እንዲሁም አካባቢና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃና ቦታን በመጠቀም አንዱ ሌላውን ለማናደድ ሆን ብሎ የሚፈጥረው ንትርክ ነው፡፡ ይህ በአብዛኛው በእረኞች አካባቢ ይታያል፡፡ እረኞች ከወንዝ ወዲያ ማዶና  ከወንዝ ወዲህ ማዶ በመሆን በቡድን ተከፋፍለው አባትን፣ እናትን፣ ወገንን፣ ዘርን፣ ፆታን ግላዊ ስብዕናን ወዘተ የሚነኩ የወዘበሬታ ግጥሞች አሏቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል እረኞችን አልን እንጅ ከተሜና ገጠሬ፣ ወንድና ሴት ወዘተ የሚወረፍባቸውም እንዳሉ አያጠያይቅም፡፡ አንዱ ሌላውን ሲነካ ሌላው ሌላውን ሲያሽሚጥጥ ቀኑን ይገፋል፡፡ "አንዱ ባንዱ  ሲስቅ ጀምበር ጥልቅ" እንዲሉ ጥሩ ምሳሌ ባይሆንም እስቲ ከእረኞች ወዘበሬታ ለምሳሌነት እንመልከት፡-

ወይኖ ወዲያ ማዶ

ወይኖ ወዲያ ማዶ

እናትህ ወለደች አባብና ዘንዶ፡፡

ይህ እናትን የሚነካ ነው፡፡ አንዱ ቡድን ወዲያ ማዶ ሆኖ ይህንን ሲሰድብ ሌላው ከወዲህ ማዶ ሆኖ ሌላ በመዝፈን ምላሹን ይሰጣል፡፡

ወዘበሬታ ከቀረርትና ከፉከራ የሚለይበት ሁኔታ አለ፡፡  ቀረርቶና ፉከራ የጀግና ማወደሻ የፈሪ ማንኳሰሻ ናቸው፡፡ በጉላ አባባል ለፈሪ ስድብ ናቸው ማለት ነው፡፡ ወዘበሬታ ግን ወገንን፣ አካባቢን፣ በመለየት እርስ በርስ አንዱ ሌላውን የሚወርፍበት ነው፡፡

እረኞች እነሱ የፈጠሩትን ብቻ ሳይሆን ከህብረተሰቡ የሰሙትን ሁሉ በሜዳ ላይ ይጫወቱታል፣ ይዘፍኑታል፡፡ ከዚህም የተነሳ አንድ ከባልና ሚስት የሰሙትን የቀልድ ግጥም በሜዳ ላይ ሲጫወቱት ይሰማል፡፡ ባል ሚስቱ አጥሚት በምትሰራበት ጊዜ ቁጭ ብሎ እየተመለከተ ሲያስቸግራት ተነስና ተኛ ትለዋለች፡፡ ባል አልተኛም ይላል፡፡ ከዚያም ሚስት የምሰራው ሙቅ ነው ትለዋለች፡፡ እርሱም ታዲያ ሙቅ እህል ነው ይላታል፡፡ እርሷም እንዲህ ካልክ እደፋዋለሁ ትለዋለች፡፡ ባል የተደፋውን እጠጣዋለሁ እያሉ ሲቀላለዱ የሰማ

እረኛ ከብቶችን ከጓደኞቹ ጋር በሚጠብቅበት ጊዜ ከሰዎች የሰማውን ቀልድ ከጓደኞቹ ጋር እርስ በርስ እየተቀባበሉ እንደሚከተለው ይቀላለዳሉ፡

ተነስተኛ

ጉልቻው ሳይተኛ

ሙቅ ነው' ኮ

እኔም አውቄ ነው'ኮ

ወንድ አይቀምሰው

እህል አይገድልም ሰው

አንስቼ አፈሰው

አጎንብሺ እልሰው፡፡

እረኞች በሰዎች ላይ የሚያዩትን ውሸት፣ ከህደት፣ እንዲሁም፣ ከአንዱ ወደ ሌላው የሚገለበጡ፣ የማይታመኑ መሆናቸውን ብዙ ጊዜ ያያሉ፡፡ እነዚህ እረኞች ከህብረተሰቡ አልፎ እነርሱ በሚውሉበት የስራ ቦታ አብረዋቸው የሚውሉ እረኞችንም ቢሆን የተነገረውን የማይደብቅ ዛሬ ከአንዱ ጋር የነበረው ነገ ከሌላው ጋር ሆኖ ሲያማውና ሲሰድበው ስለሚያዩ እርስ በርስ ይተዋወቃሉ፡፡ ይህን ከህብረተሰቡ የወሰዱትን ወይም በስራ ቦታ ያጋጠማቸውን ያለመታመን ችግር በቀልድ መልክ እንደሚከተለው በላሜ ቦራ ግጥም ይገልፁታል፡፡

ላሜ ቦራ

እንች እንጀራ

የዳጉሣ

ቢያንቀኝሳ

እግዜርሳ

እግዜርማ

ቆላ ወርዶ

ተወራርዶ

ላሚቷ ጥቁር

ወተቷ ነጭ

የዘንድሮ ሰው ተገላባጭ፡፡

ይህን የቀልድ ግጥም ሲዘፍኑ እርስ በእርስ እየተቀባበሉ ነው ፡፡ እረኞች በመካከላቸው እንደዚህ አይነት ባህሪ ያለበትን ልጅ በግጥም መልክ ከላይ እንደተገለፀው ይነግሩታል፡፡

በአካባቢው ውስጥ ያሉሰዎች የሚመገቡት ምግብ ያገኙትን ቤት ያፈራውን ሁሉ ነው፡፡ ይህም የተገኘውን ምግብ ድንች፣ ንፍሮ፣ ጐመን ሌላም ሌላም ይመገባሉ፡፡ ከዚህ የተነሳ ሙጀሌ የያዛቸው ሰዎች ይህን ያመጣባቸው የሚመገቡት ምግብ ነው ከምንመገበው ምግብ የተነሳ ነው በማለት በምግቡ ላይ እንደሚከተለው በስድብ ግጥማቸው ይገልፃሉ፡፡

አሰሱን ገሰሱን የበሉት እንደሆን
እሱ ነው መሰለኝ ሙጀሌ የሚሆን፡፡

በአካባቢው ብዙ መሬት ያለው ነገር ግን ጉልበቱ ከመድከሙ የተነሳ መሬቱን ማረስ ያልቻለ ሰው መሬቱን ማረስ ለሚችል ሰው በመስጠት አዝመራውን እኩል ይካፈላሉ፡፡ ወይም በጉልበታቸው ተማምነው መስራት በሚቻልበት ቦታ ሁሉ እየተዘዋዋሩ የሚኖሩ ሰዎች በአካባቢው በብዛት አሉ፡፡ እነዚህን ሰዎች የተመለከቱት እረኞች በሚጫወቱበት ጊዜ ልክ እንደ እርሱ እየተዘዋወርኩ እኖራለሁ፡፡ ጉልበት ካለኝ እሄዳለው የሚለውን መልዕክት ለማስተላለፍ ይጠቀሙበታል፡፡ ይህንን ግጥም በብዛት የሚጠቀሙት በችግር ምክንያት ኑሮ የመረራቸው፣ ትዳር መያዝ ያልቻሉ ሰዎች ናቸው፡፡ ከነዚህ ሰዎች የሰሙትን እረኞች በከብት ጥበቃ ወቅት እንደሚከተለው በዜማ ይዘፍኑታል፡፡

ሚስትም አላገባ ላሳብም አልቸኩል
የደከመ እያየሁ እገባለሁ የኩል፡፡

በአካባቢው የአንድን ወንድ ሚስት ሌላሰው እንዲሁም የአንዷን ባል ሌላ ሴት ውሽማ ማድረግ የተለመደ ነው፡፡ ይህ ነገር በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ባይኖረውም እንኳን አንዳንድ ሰዎች ሲያደርጉት ይታያል፡፡ ከዚህ የተነሳ ውሽማ በተባለው ሰው ምክንያት ከባሏ ውጭ የምትሄድ ሴት እንዲሁም ወንዱ ትዳራቸውን ያጣሉ፡፡ ይህንን ሚስጥር የሚያውቁ የአካባቢው እረኞች ሴቷን ውሽማሽ ሲመጣ ሰዎች በሚያዩበት ሁኔታ አድርጊ ለማለት እርሷን ሲያዩ ወይም በቤቷ አካባቢ ከሆኑ በቀልድ መልክ እንደሚከተለው ይላሉ፡፡

አትጣይ ከባልሽ ቤትሽ አይፈታ

ስርቅ አርገሽ ስጭኝ የኔንየኔን ፈንታ፡፡

እረኞች ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የተሰጡትን ምግብ ይበላሉ፡፡ በአካባቢው ውስጥ ያሉልጆች ለእነርሱ ብቻ የሚዘጋጅ ምግብ የላቸውም፡፡ ስለዚህ እናቶቻቸው የሰጧቸውን ምግብ የመብላት ግዴት አለባቸው፡፡ የተሰጡትን ምግብ አንበላም ካሉ ይቆነጠጣሉ ወይም ይገረፋሉ፡፡ ይህንያዩ እረኞች ምግብ ይዘው ሜዳ በሚበሉበት ጊዜ አልጣፈጠኝም ማለት የለም፡፡ በዚህ ጊዜ ምግቡ ተመሳሳይ ከመሆኑ የተነሳ ሰለቸኝ ብሎ የሚያጉረመርም ካለ ጓደኛው ምግቡን ባለመብላቱ ምን ሊያስከትል እንደሚችል ይገልፅለታል፡፡

ትበላ እንደሆን የሰጡህን ብላ

ደግሞ እንደ እገሌ ትቀምሳለህ ዱላ፡፡

ሰዎች ለሰዎች ብዙ ጊዜ ታማኞች አይሆኑም፡፡ በተለይ የሚያጓጓ/የሚያሳሳ/ ነገር ካገኙ ለዚያ ነገር ታማኞች አይሆኑም፡፡ ከዚህ የተነሳ እረኞች ከብት በሚጠብቁበት ጊዜ የያዙትን ምግብ ወይም ሌላ ነገር ለጓደኞቻቸው እንዲጠበቅ ሊሰጡት ይችላሉ፡፡ ይህ የሚሆነው ከብት ሊመልሱ ሲሄዱ ወይም ለጨዋታ ሲሯሯጡ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የተሰጠውን አደራ መጠበቅ ያልቻለው እረኛ የጓደኞቹን ነገር ተጠቅሞበት ይጠብቃቸዋል፡፡ ከዚህ በታች የተዘፈነው ግጥም በቀልድ መልክ እንደዚህ አይነቱን መልዕክት ቢይዝም እንኳን ብዙ ጊዜ በእረኞች ዘንድ ብቻ ሳይሆን በትምህርት ቤት ውስጥ ልጆቹም ይዘፍኑታል፡፡ ግጥሙ ከላይ የተጠቀሰው ሀሳብ በእረኞችም በህብረተሰቡም ዘንድ የሚያሳይ ቢሆንም በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ በእረኞች ዘንድ ከላይ የተጠቀሰውን ሃሣብ ለመግለፅ ብለው አይጠቀሙብትም፡፡ ነገር ግን በትምህርት ቤትም ሆነ በእረኞች ዘንድ እንደ መዝናኛ ወይም መጫወቻ ስለሚቆጥሩት ይዘፍኑታል፡፡

እኔ ቀበሮ ቀብራራ

ሥጋ እበላለሁ ጨጓራ

ሚስቴ ሆናብኝ አራስ

አምጣልኝ ብላኝ ምላስ

ከቤቴ በላይ ስደርስ

እኔው ብሶብኝ ጉርስ

እየረሳሁት ጉርስ፡፡

ከዚህ በታች የቀረበው ግጥም በውስጡ ብዙ ነገሮችን ያካተተ በመሆኑ ሰዎች እርስ በርስ እስኪገዳደሉ ያደረሰ ሚስጥራዊ ግጥም ነው፡፡ ግጥሙ ቀልድ ቢመስልም ስድብን፣ ንቀትንና ሌላም ሀሳብ በውስጡ የያዘ በመሆኑ ሰዎች እርስ በርስ እየተቀባበሉ ይሰዳደቡበታል፡፡ ይህ ግጥም በህብረተሰቡ ውስጥ ትልቅ የተባሉ ሰዎች ሲጠቀሙበት ይታያል፡፡ ይህን የሰሙት እረኞች ደግሞ ሰዎችን በመሳደብ፣ ዝቅ በማድረግ እንደሚከተለው የዴ በለኝ የዴ በማለት በአካባቢያቸው ይሰዳደባሉ፡፡ ይህ የሚሆነው ጠያቂና ተጠያቂ ባሉበት ነው፡፡

የሻበለኝ የሻ፤

የሻ፡፡

ልትሳደብ ነው ኬሻ?

የዴበለኝ የዴ፤

የዴ፡፡

አህያ ተጭና ትሄዳለች እንዴ?

የዴበለኝ የዴ፤

የዴ፡፡

የደጋ ዳሞት ሰው መናጢ ነው እንዴ?

## 3.5. ብሶትን የሚገልፁ ግጥሞች

የሰውልጅ በህይወት ዘመኑ ችግሮች ይፈራረቁበታል፡፡ እነዚህን ችግሮች በተለያየ ጊዜ ከሚገኝበት የኑሮ ደረጃ ጋር በማዛመድ በየስራ ቦታው በእንጉርጉሮ፣ በዘፈን፣ በፉከራና በቅረርቶ ብሶቱን ያሰማል፡፡ በሚሰራበት የስራ ቦታ ሁሉ በውስጡ የታመቀውን ብሶትና ወደፊት ይሆናል ብሎ የሚገምተውን ችግር ከአዕምሮው አውጥቶ በመናገሩ ከችግሩ የተላቀቀ እየመሰለው ይረካል፡፡ በመሆኑም እረኞች በስራ ቦታቸው ላይ የሚያዜሟቸው ዜማዎች በተለያየ መልኩ ቅሬታና ብሶትን የሚገልፁ ናቸው፡፡

እረኞች ብዙጊዜ ከሰው ቤት ተቀጥረው ይሰራሉ፡፡ እነዚህ እረኞች ተቀጥረው በሚሰሩበት ቤት የሚደርስባቸውን በደል በስራ ቦታው ከብቶችን እየጠበቁ በእንጉርጉሮ ይገልፃሉ፡፡ እነዚህ እረኞች ከብቶችን ሩቅ ቦታ ይዘው የሚሄዱ ከሆነ በጠዋት ተነስተው ለእነሱ ምግብ አይሰሩላቸውም፡፡ በጠዋት ሳይበሉ ከብቶችን ይዘው ይሄዳሉ፡፡ ምሳ

የሚላክላቸው ከራባቸውና ከደከማቸው በኋላ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ በርሃብ አንጀቱ ተስቦ መሰቃየቱን ቅሬታና ብሶቱን እንደሚከተለው ይገልፃል፡፡

የሰው ቤት እንጀራ ምንቢጋገር ብዙ
ሳይርብ አይገኝም ሳይቅበዘበዙ፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ከሰው ቤት ተቀጥሮ የሚሰራ በችግር ምክንያት እራሱን ሳይችል ቀርቶ የሰው አገልጋይ በመሆኑ ያዝናል፡፡ የቀጠሩት ሰዎች እንደ እናትና አባት ተመችተው ሊይዙት አይችሉም፡፡ እረኛው ቀኑን ሙሉ ከብት ሲያግድ ይውላል፡፡ በአጨዳ ወቅት ያጭዳል፣ ያበራያል፣ ያርማል፣ እነዚህን የመሳሰሉ ስራዎችን ይሰራል፡፡ በመሆኑም ሰዎቹ ልፋቱን በሙሉ ከንቱ ያደርጉታል፡፡ የሰራ አይመስላቸውም፡፡ በዚህ ጊዜ ከብቶቹን እየጠበቀ ቅሬታና ብሶቱን እንደሚከተለው ይገልፃል፡፡

ውሃ ወርዶ ወርዶ መቆሚያው አባይ
እናት ወልዳ ወልዳ ለሰው አገልጋይ
እውሃ ቢዶሉት አይሚሚም ኩብት
አይመሰገንም የድሃጉልበት፡፡

እረኛ በአካባቢው ነዋሪ ዘንድ ዝቅያለ ቦታ የሚሰጠው በመሆኑ ለእረኛ ተብሎ ምግብ አይሰራም፡፡ እረኛ ቤት ያፈራውንና የተገኘውን በልቶ ይውላል፡፡ ለእረኛ ተብሎ ወጥ አይሰራም፡፡ ወጥ ከቤት ውስጥ አልቆ ከሆነ በአዋዜ /ድልህ/ ተደርጐ በደረቅ እንጀራ ይሰጠዋል፡፡ ይህ አዋዜ መደጋገሙ ያሰለቸው እረኛ የውስጡን እንደሚተለው በእንጉርጉሮ ቅሬታና ብሶቱን ይገልፃል፡፡

ማታ በጨው በላሁ እንዲያው በደረቁ፣
ምሳ በጨው በላሁ እንዲያው በደረቁ
የሰው ቤት እንጀራ ይሄነበር ጠንቁ፡፡
እራቡና ጥሙ በዛብኝ ሁልጊዜ
የሚቀርበው ምግብ ወጥ የለው አዋዜ፡፡

ወጥ የሌለው እንጀራ ምን የህል የሚሰለችና የሚያስመርር እንደሆነ የሚያሳማ አይደለም፡፡ ወጡ ቢቀር በሌላ ማባያ ማቅረቧን ትታ ያለምንም ተጨማሪ ነገር ደረቅ እንጀራ የምታቀርብለትን አሰሪ የሚገልፅ ነው ከፍብሎ በሁለተኛነት የተገጠመው ግጥም የሚያሳየን፡፡

እረኞች በሰው ቤት ተቀጥረው በሚሰሩበት ጊዜ እንደ እናት ቤት መብላት መጠጣት አይችሉም፡፡ በአካባቢው ውስጥ ከሚገኙ ሰዎች አንዳንዶቹ እግዜአብሔርን በመፍራት እንደ ልጅ ሊያዩዋቸው ይችሉ ይሆናል፡፡ እናት ከታጣ እንኳን ያላትን ሳታዳላ ለልጇ ትሰጣለች፡፡ እረኞች ከተቀጠሩበት ቤት ውስጥ እንደልጆች እኩል ምግብ አይሰጣቸውም፡፡ ለልጆች ትልቅ ነገር ሲሰጣቸው ለእረኞች ትንሽ ሆኖ በዚያ ላይ የልጆች ትርፍራፊ ይሰጣቸዋል፡፡ እነዚህ እረኞች በሰው ቤት እስካሉ ድረስ የሰው እናት ነች የምታስተዳድራቸው፡፡ በዚህም ምክንያት እረኞች ምግብ ሲበሉ ሆዳሞች ተብለው በልጆች ወይም በእናታቸው ይሰደባሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የከፋው እረኛ ብሶቱን የሚናገረው እንደሚከተለው በእንጉርጉሮ ቅሬታና ብሶቱን ይገልፃል፡፡

እህቴ ትፍጭና እናቴ ትጋግረው
ይህን በልቷል ብላ የማትናገረው፡፡
አንች የሰው እናት ይብላሽ አረመኔ
ትኩሱን ለልጅሽ ያደረውን ለኔ፡፡
አንች የሰው እናት ጠባይሽ ወለላ
አይቡን ለልጆችሽ አጓቱን ለእረኛ፡፡

# ማጠቃለያ

በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች በተናጠልም ሆነ በቡድን የተለያየ ሀሳብን ለመሰንዘር ቢችሉም አጠቃላይ የሆነ ምርኩዛቸው ግን የሚኖሩበት ህብረተሰብ ነው፡፡ እረኞች ጉዟቸው፣ አመለካከታቸው፣ አስተሳሰባቸውና አሰራራቸው እረኞች እንደፈለጉት አፈንግጦ ሊሄድ የማይችል ነው፡፡ እረኞች ሜዳ ላይ ሆነው የሚዘፍኑት/የሚገጥሙት/ ግጥም ከማህበረሰቡ የወጣ የተነገረ ሲሆን ማህበረሰቡ ለመግለፅ፣ ለመናገር ያልደፈረውን እነሱ በስራ ቦታቸው ያወጡታል፡፡ ይህ ሲሆን ነፃነት ይኖራቸዋል እንጅ ከማህበረሰቡ ሀሳብና ድርጊት ያፈነገጠ ግን አይደለም፡፡ የሚናገሩት፣ የሚዘፍኑት በማህበረሰቡ ውስጥ የተመለከቱትን ነው፡፡ ሆኖም ብዙ ጊዜ ሜዳላይ በነፃነት የሚናገሩትን በቤት አካባቢ ለመናገር አይደፍሩም፡፡ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ በማህበረሰቡ ዘንድ የተጠላና ነውር የሆኑ ነገሮችን ሊያነሱ ስለሚችሉ ነው፡፡

ከእነዚህ እረኞች የተሰበሰቡት ግጥሞች የደጋ ዳሞትን ህብረተሰብ አጠቃላይ ህይወት የሚዳስሱ ናቸው ማለት አያስደፍርም፡፡ ህብረተሰቡ በነጋ በጠባ አሰራሩንና አመለካከቱን የማለያይበት ስነቃሎች እንዳሉት እሙን ነው፡፡ ምክንያቱም ከማህበረሰቡ አንዱ ክፍል ብቻ በጨዋታ መልክ ያነሳውን ጉዳይ፣ ሁሉንም ነገር አጠቃሎ ይዟል ለማለት አያሰደፍርም፡፡

ጥናቱ ያካተታቸው ግጥሞች የደጋ ዳሞትን ህብረተሰብ አጠቃላይ ህይወት ባይገልፅም በተወሰነ መልኩ የእረኞችንና የህብረተሰቡን ህይወት ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የደጋ ዳሞት ወረዳ የእረኞችን ስነቃል አሰባስቦ ለተተኪው ትውልድ ለቅርስነት ለማቆየት ተሞክሯል፡፡

# ሙዳየ ቃላት

| | |
|---|---|
| ለከት | ወሰን የሌለው |
| ለምድ | የበግ/የፍየል/ቆዳ |
| ማንጓት | ጀራፍ ማጮህ |
| ሙርጥ | ቂጥ |
| ሙጃ | የሳር አይነት |
| ሸንብርማ | የቀበሌ ስም |
| ንሳ | ውሰድ/ ተቀበል/ |
| ቶፋ | ከሸክላ የሚሰራ የድንች ወይም የንፍሮ መቀቀያ |
| አጓት | የወተት አይነት፣ ወተት ከተናጠ በኋላ ቅቤውን ካወጡ በኋላ በእሳት ሲሞቅ የሚወጣ ውሃ |
| ኩታ | ነጠላ |
| ወሸ | አህያ |
| ደንደስ | ማጅራት |
| ድግር | የእርሻ መሳሪያ በጐንና በጐን ሁለት ቀዳዳ ያለው አፋ የሾለ ማረሻና ሞፈር የሚያያዝ |
| ጉድባ | ጫካ/በሳር የተሸፈነ አካባቢ/ |

# ዋቢ መፃሕፍት

ሚሊዬን ስዩም/1973/ "የገበሬውን ሙያና ኑሮ የሚያንፀባርቁ የአማርኛ ግጥሞች"፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጰያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለትምህርት፤ ዲማጽ፡፡

ሞላፈለቀ/1993/ "በደምበጫ አካባቢ የሚሰሙ የውቂያ ግጥሞች ስነ ቃላዊ ባህርያትና ይዘት"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፡፡

በሺር ፈለቀ/1982/ "የጊምባ አረኞች የሚያስሟቸው ግጥሞች"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፡፡

ባዩ መኩሪያ/1976ዓ "በደብረማርቆስ አውራጃ የገበሬውን የስራ ሁኔታ እንቅስቃሴ የሚያንፀባርቁ ባህላዊ ግጥሞች"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጰያ ቋንቋዋችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፤ ዲማጽ፡፡

ተኸላይ ትዕዛዙ/1990 "የአክሱምና አካባቢዋ አረኞች የሚያስሟቸው የዘፈን ግጥሞች"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፤ ዲማጽ፡፡

ዘሪሁን አስፋው/1992ዓ "<u>የስነጽሑፍ መሰረታዊያን፤</u> አዲስ አበባ ማተሚያ ቤት

ፈቃደ አዘዘ/1991/ <u>የስነቃል መምሪያ፤</u> አዲስ አባ ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም፡፡

Ruth, Finnegan(1982) <u>oral Literature in Africa</u>, London oxford university press.

– – – (1977) <u>oral poetry</u> London Cambridge University. Press.

## አባሪ አንድ

### 1. የጅራፍ ግጥሞች

1. የአንተ ጅራፍ ለከስካሳ
   የኔ ጅራፍ አንበሳ
   ስማውስማው ሲያሳ፡፡
2. የአንተ ጅራፍ ስትቆረጥ
   በኔ ለመድረስ ወገብህ አይቆረጥ፡፡
3. ንሳ ተቀበል የጅራፌን መልዕክት
   መስከረም ጠባ ስትዞር ለከት
   ብታስታውሰው አብቧል ሙጃ
   እንግዲህ ይብቃህ ያለው ምድጃ፡፡
4. ንሳ ተቀበል የጅራፌን ጩኸት
   ቡሃቃውን አምጣ ከትሺ ማጀት
   ታች ምድጃ ስጣት ለናትህ
   ስታነኳኩር እንድታጕርስህ
5.

### 2. የአህያ መጣች ግጥሞች

6. አህያ መጣች ተጭና ወንበር
   እጣን አሮጌው ይቀጠፍ ጀመር፡፡
7. አህያ መጣች ተጭና ገብስ
   ምን የማሉት ነው መሬት ማውረስ፡፡
8. አህያ መጣች ተጭና ኩታ
   ያጓደኛየ ሆዱ ገበታ፡፡
9. አህያ መጣች ተጭና ለምድ
   ያጓደኛየ ማዞሪያ ሆድ፡፡
10. አህያ መጣች ተጭና ጋሻ
    ያጓደኛየ የመንደር ውሻ፡፡
11. አህያ መጣች ተጭና ዳባ

እገሊት ሄደት ጉድባለጉድባ፡፡

12. አንተ አያ እገሌ የእንትና ባል
ሚሽትህን ጠብቅ አትበል ቸል፡፡

13. እንዲህ ተሆነ የባል ስራቱ
ቶሎ ቶሎ በል ይቅረብ እራቱ
እግሯንም አጥበህ አደስ ቀብተህ
ላክለት እንጂ ላአያ ውሽሜ
ለሜዳ አህያ ላያ ሽምሽሜ፡፡

14. አህያ መጣች ተጭና ሙሬ
ከጉድጓድ ገባ ሲሰርቅ በሬ፡፡

15. አህያ መጣች ተጭና ፊጦ
አበሻ መጣ ዱላውን መልጦ
እንትና ሮጠ ቂጡን ሽምጥጦ፡፡

**3. የወዘበሬታ /የቀልድ/ ግጥሞች**

16. ወይኖ ወዲያ ማዶ
ወይኖ ወዲያ ማዶ
እናትህ ወለደች እባብና ዘንዶ፡፡

17. ተነስተኛ
ጉልቻው ሳይተኛ
ሙቅ ነው' ኮ
እኔም አውቄ ነው' ኮ
ወንድ አይቀምሰው
እህል አይገድል ሰው
አንስቼ አፈሰው
አጎንብሺ እልሰው፡፡

18. ላሜ ቦራ
እንቺ እንጀራ
የዳጉሳ
ቢያንቀኝሳ

እግዜርሳ

እግዜርማ

ቆላወርዶ

ተወራርዶ

ላሚቱ ጥቁር

ወተቷ ነጭ

የዘንድሮ ሰው ተገላባጭ።

19. አሰሱን ገሰሱን የበሉት እንደሆነ

እሱነው መሰለኝ ሙጀሌ የሚሆን።

20. ሚስትም አላገባ ላሳብም አልቸኩል

የደከመ እያየሁ እገባለሁ የኩል።

21. አትጣይ ከባልሽ ቤትሽ አይፈታ

ስርቅ አርገሽ ስጭኝ የኔን የኔን ፈንታ።

22. እኔ ቀበሮ ቀብራራ

ስጋ እበላለሁ ጨንገራ

ሚስቴ ሆናብኝ አራስ

አምጣልኝ ብላ ምላስ

ከበቴ በላይ ስደርስ

እኔው ብሶብኝ ጉርስ

እየረሳሁት ጉርስ።

23. ትበላ እንደሆን የሰጡህን ብላ፣

ደግሞ እንደ እገሌ ትቀምሳለህ ዱላ።

24. ከሰው አገር ሄዶ ደህና ከመበደር

እንቅርታም አግብቶ እንደጊዜው ማደር

25. ጉስር ተነሳና ጥጆቹን አስወጣ

ላንተም ይሻልሃል አሬራ ብትጠጣ።

26. የማይሆንልኝን የሰው ገረድ ስሜ

ከባቄላው ጋራ ሲፈጭ ያድራል ስሜ።

27. የዴ በለኝ የዴ

የዴ

አህያ ተጭና ትሄዳለች እንዴ?

28. የሻ በለኝ የሻ

የሻ

ልትሳደብ ነው ኬሻ?

29. የዴ በለኝ የዴ

የዴ

የደጋ ዳሞት ሰው መናጢ ነው እንዴ?

## 4. ብሶትን የሚገልፁ ግጥሞች

30. የሰው ቤት እንጀራ ምን ቢጋገር ብዙ

ሳይርብ አይገኝም ሳይቅበዘበዙ፡፡

31. ውሃ ወረዶ ወርዶ መቆሚያው አባይ

እናት ወልዳ ወልዳ ለሰው አገልጋይ፡፡

እውሃ ቢደልቱት አይሚሚም ኩበት

አይመሰገንም የደሃ ጉልበት፡፡

32. ማታ በጨው በላሁ እንዲያው በደረቁ

ምሳ በጨው በላሁ እንዲያው በደረቁ

የሰው ቤት እንጀራ ይሄ ነበር ጠንቁ፡፡

33. እራብና ጥሙ በዛብን ሁልጊዜ

የሚቀርበው ምግብ ጨው የለው አዋዜ፡፡

34. እህቴ ትፍጭና እናቴ ትጋግረው

ይህን በልቷል ብላ የማትናገረው፡፡

35. አንች የሰው እናት ይብላሽ አረመኔ

ትኩሱን ለልጅሽ ያደረውን ለኔ፡፡

36. አንች የሰው እናት ጠባይሽ ወለላ

አይቡን ለልጆችሽ አጓቱን ለእረኛ፡፡

## 5. የእንኳ ስላንትያ ግጥሞች

37. ጠያቂ እንካስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በቆርበት

ተጠያቂ ምናለ በቆርበት

ጠያቂ ጉንጭህ ተወጥሯል ቅማል የሞላበት፡፡

38. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በደንደሮ

ተጠያቂ ምን አለ በደንደሮ

ጠያቂ እናትክን በዳልህ አይጡ ተንደርድሮ፡፡

39. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በሳንቃ

ተጠያቂ ምናለ በሳንቃ

ጠያቂ እናትህ ሞተች በእምሷ ፀጉርታንቃ፡፡

40. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በቋት

ተጠያቂ ምናለ በቋት

ጠያቂ እናትህ ሞተች አሯ ደርቆቧት፡፡

41. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በጠላ

ተጠያቂ ምናለ በጠላ

ጠያቂ ከጉብሉ ሁላ አንተነህ ጠልጣላ፡፡

42. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በማርዳ

ተጠያቂ ምናለ በማርዳ

ጠያቂ ከጉብሉ ሁላ አንተነህ ወራዳ፡፡

43. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በሻማ

ተጠያቂ ምን አለ በሻማ

ጠያቂ አባት ሞተ ንፍሮ ሲሻማ፡፡

44. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በቡትት

ተጠያቂ ምን አለ በቡትት

ጠያቂ አባትህ ሞተ ቂጣ ሲጎትት፡፡

45. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በኮሶ

ተጠያቂ ምን አለ በኮሶ

ጠያቂ እናትህን በዳልህ ድንበር አንተርሶ
አባትህ ወረደ የእንግዴ ልጅ ለብሶ፡፡

46. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በሰማይ ዳር ቡቃያ

ተጠያቂ ምን አለ በሰማይ ዳር ቡቃያ

ጠያቂ እናትህ ወለደች ቦቃ ቦቃ አህያ፡፡

47. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በአሎሎ

ተጠያቂ ምን አለ በአሎሎ

ጠያቂ በባትህ ለበሰ የአህያ ደበሎ፡፡

48. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በወንፊት

ተጠያቂ ምን አለ በወንፊት

ጠያቂ ማታ ይቆይሃል የሙጀሌ ፍትፍት፡፡

49. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በአጥር ቁንጮ

ተጠያቂ ምን አለ በአጥር ቁንጮ

ጠያቂ አባትህ አገባ የዝንጀሮ ቆንጆ፡፡

50. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በወይራ ስራ ስር

ተጠያቂ ምን አለ በወይራ ስራ ስር

ጠያቂ የአባትህ ቁላ መቶ ፍየል ያስር፡፡

51. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በአገልግል

ተጠያቂ ምን አለ በአገልግል

ጠያቂ አንተ ሙት እና እኔ ላገልግል፡፡

52. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በሜዳ

ተጠያቂ ምን አለ በሜዳ

ጠያቂ አባትህ ይሮጣል ቀበሮ ሊበዳ፡፡

53. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ በጭድ

ተጠያቂ ምን አለ በጭድ

ጠያቂ እናትህ ወለደች አስራ ሁለት ማጭድ፡፡

54. ጠያቂ እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ በምንትያ

ጠያቂ		በአረቂ

ተጠያቂ		ምን አለ በአረቂ

ጠያቂ		አውቄብሃለው አንት ወደላ ፋቂ፡፡

55. ጠያቂ		እንካ ስላንትያ

ተጠያቂ		በምንትያ

ጠያቂ		በሞፈር

ተጠያቂ		ምን አለ በሞፈር

ጠያቂ		ወስዶ ይጨምርህ ከሚካኤል አፈር፡፡

## 6. ልዩ ልዩ ግጥሞች

56. እከሌ ጉጥር የጐመን እጥር

57. ስትሄድ ቅትርቅትር ስትበላ እንዳንበጣ
    ወዘና የሌለህ ትመስላለህ ቋንጣ፡፡

58. ባልአገባሁ ብላ የሽንኩርት እራስ
    እሱም በዛብሎ ወሰደው ንፋስ፡፡

59. የበጐች እረኛ አመዳም ቅርናታም
    የከብቶች እረኛ ውብ አንገተ መልካም፡፡

60. የፍየል እረኛ ፎከቶፎከቶ
    የከብቶች እረኛ ሽጋው ተጐልቶ፡፡

61. እኔ ምንቸገረኝ ጨረቃ ባትወጣ
    ታበራልኛለች የእንትና መላጣ፡፡

62. እከሌ ዝጫ ያጓት መገልበጫ

63. የእኔማ እከሌ የወገራ በሬ
    ከሆዱ ላይ ብቆም ይታያል አገሬ፡፡

64. የቂጥክን ስባቱን እጅግ አትውደደው
    ሱሪህ በተሰፋ በወሩ ቀደደው፡፡

65. የሰው ነወይ የከብት እዩት ይህን ደንደስ
    የበላ አይመስልም ወይ አስር አጋሰስ፡፡

66. እገሌ

አቤት

ይጠራሃል መሬት

አገሌ ያሉህ

ሙርይ ይነቅህ

ሙርይ ተራ ተራ

የሰማይ ደብተር

ወፊቱ ወፊቱ

ልጅ የሌለሽቱ

ልጅማ ነበረኝ

ሞቱ ወሰደብኝ

ሞቱ በደለኛ

ያዙልኝ በዳኛ

ያባቴ በሬ ቀንዱ በርበሬ

የናቴ በሬ ሻኛው አሞሌ

ሞሰቤ ተሽከረከረች

ዓባይ ደሜ ተነከረች፡፡

67. ነይ እንሂድ ዋሻ ለዋሻ

አበላሻለሁ የሞተች ውሻ፡፡

68. ነይ እንሂድ ጎሬ ለጎሬ

አበላሻለሁ እባብ ጎርጉሬ፡፡

69. ነይ እንሂድ ጓሮ ለጓሮ

አበላሻለሁ የገማች ዶሮ፡፡

70. ነይ እንሂድ ገደል ለገደል

አበላሻለሁ የገማች ጊደር

71. እዋ በቀለች

እማማ ቶሎ ነይ

በቶሎ ነይ ቀይ

በቀይ ላቀች

በላቀች ደመቀች

በደመቅ ይደነቅ

በይዱ ስንዱ

በስንድ የላም ድድ

በላም ልማም

በልማም ነጭ ላም

በነጭ ምላጭ

በምላጭ ሰው ይላጭ

በሰው ካሳው

በካሳው ቢረሳው

በቢረስ ዲያብሎስ

በዳቢል ፈንታ ቢል

በፈንታ ኮትና ቡታንታ

በኮት መስኮት

በመስኮት የና ኮት

በደና ጎዳና

በጎዶ ሞሀዶ

በሞሀድ አያልነሽ

በአያልነሽ ቆብ የለሽ

በቆብ ቁልቋል

በቁልቋል ማን ያውቃል

ደርግ ያውቃል

በደርግ ማረግ

በማረግ የሻረግ

በየሺ ተነሽ

በተነሽ ደመላሽ

በደም ሰላሜ ትውደም

በየሺ ኧረ የሺ የሺ

ከታች መደብ ሆነሽ

እምሱን አምሺ
የእንቅቡ ሲያልቅብሽ
ከጎታው እፈሺ
የጎታው ሲያልቅብሽ
ወደ ሰማይ ፍሺ
የግብር መሬቴን እንዳታበላሺ፡፡

72. በበሮች አምላክ በኩሊ በፋና
በላሞችሽ አምላክ በነወንዝ አደራ
በቀሚስሽ አምላክ በጥልፋ በጥልፋ
በጭኖችሽ መሀል ይውሰደኝ እንቅልፋ፡፡

73. የቡዳ መድኃኒት በክንድሽ አስረሽ
አንተርሽኝና ልለፍልፍልሽ፡፡

74. እስኪ በስመአብ ብዬ ልጀምር ጸሎት
ትመጣልኝ እንደሁ ስደግም ዳዊት፡፡

75. ሚስትም አላገባ ላሳብም አልቸኩል
ያባወራውን ሚስት እይዛለሁ የኩል

76. የሰው ሚስት አልነካም አልገባም ኩነኔ
ሁለት ሳምንት ለሱ ወር ከሳምንት ለኔ

77. አባትዬው ክፋ የድግር እላቂ
እናቲቱ ክፋ የእንጨት ስንጣቂ
ልጅቱ ናት እንጂ ንግግር ዐዋቂ፡፡